# በቤተ-ክርስቲያን ላይ ያደረሱት ጉዳት

በዚህ ገዳም ውስጥ በቤተ ጳጳ ጎብረት ውስጥ እየመነኮሱ በመውጣት ያንኑ የከፋ ክሕደታቸውን እንደያዙ በአስተዳዳሪነት በቅስናና በዲቁና በቅዳሴ መምህርነትም በየቦታው እየተመደቡ እየሠሩ ይገኛሉ። እነኝህ ሰዎች ከዚች ቤተ ክርስቲያን ጋር ምንም አይነት ዝምድና ስለሌላቸው ጥቅማቸውን እንጂ ጥቅሟን እንደማይፈልጉ መታወቅ አለበት ዕገሌና ዕገሌ ብለን እስከማንቆጥራቸው ደርሰው አዲስ አበባን በሙሉ የተቆጣጠሯት እነሡ እንደሆኑ ከገዳሙ መነኮሳት የተነገረንና የተሰጠን መረጃ አስተማማኝ ነው። ለቤተ ክርስቲያን የወንጌል እንቅስቃሴ ደፋ ቀና ስንል ተሐድሶ መናፍቅ ተብለን ከመድረኩ ስንገለል እንደ ሐዋርያትና እንደ ነቢያትም ስለሰበክን እንደ ተቃዋሚ ተቆጥረን ይቅርታ ብንጠይቅ እንኩዋ ከገባን የከሐዲዎችን አከርካሪ ስለምንሰብር መልስ ተነፍገን እስከአሁን በደጅ አለን።

ነገር ግን እኛን የገፋንና ለጥያቄዎቻችን መልስ መስጠት የተሳናቸው እነሡ እግዚአብሔር ሦስት ነው ሦስት አምላክ አለን ለሦስቱም አምላኮቻችን ሦስት ሦስት መለኮት በአጠቃላይ ለሦስቱ ዘጠኝ መለኮት አላቸው ብለው የሚያምኑ ቡድኖች ናቸው። ስማችን በጋዜጣና በመጽሔት እንደሌባ ሲወጣ ድንጋይና ዱላ ያቀበሉት አባቶች ሰዎች ሊደበድቡን ሲከቡን ድንጋይና ዱላ ባርከው የሰጡ አባቶች መጋረጃው ሲገለጥ እነሡ ራሳቸው ፊጽሞ የማንደፍረውንና የምንፈራውን ክሕደት በጉያቸው አስቀምጠውት አገኘናቸው እነዚህም ሰዎች ቤተ ጳጳ ከተባለው ክፍል የመነኮሱ ናቸው።

ከእነዚህም መካከል፦ ብፁዕ አቡነ አረጋዊ
ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ
ብፁዕ አቡነ ኤጲፋንዮስ

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ
አባ ተከስተ ወ.ዘ.ተ ይገኝበታል ::

እነዚህ ሰዎች በአሁኑ ሰዓት ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን በመያዝ በቤተ ክርስቲያኗ ላይ ጥቅም አሊያም ጉዳት እያደረሱ ነው:: ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች ከዚህ ከፍተኛ ማዕረግ የደረሱት ጀርባቸው ተጠንቶ አይደለምን ? ጵጵስና የሰጠው አካልስ ማን ነው ? በጎ ጎሊና ያለውና ትክክለኛ አርቶዶክስ አባት ካለ ለምን ጉባዔ አይጠራም ? ነገሩስ ለምን አይመረመርም ? ዋልድባስ ለምን መፍትሔ አያገኝም?

እንደነዚህ አይነት ሰዎችስ እየጻፉ የሚያስቀምጧቸው ትምህርቶች የኋላ ኋላ ጉዳት አያደርሱብንምን ? / ዛሬ እንደሚያነቃቅፉን አዋልድ መጻሕፍት ማለቴ ነው/ ቤተሰብነትና ወዳጅነት ለአኪላስም አልጠቀመውምና የቤተ-ክርስቲያናችን ጉዳይ በእጅጉ ሊታሰብበት ይገባል:: በቅርብ ሆነን ስንመለከተው የአንዳንድ ሰዎች ሁኔታ ከዝምድና ጋር የተያያዘ በመሆኑ ኃላፊነታቸውን በመዘንጋት በቤተ-ክርስቲያኒቱ ላይ እንዲህ አይነት ሰዎች ሲቀመጡ ትኩረት አይሰጡትም በዚህም ዓይነት ተመቻችተው ይቀመጣሉ::

ግን በነዚህ አባቶች እጅ የተሳለምን እኛ በነሱ እጅ የተባረከ ታቦት የተቆረበ ቁርባን በእነሱ እጅ የተጠመቀ ክርስቲያን በእነርሱ እጅ የመነኮሰ መነኩሴ በእነርሱ እጅ የተቀበልነው ቅስናና ዲቁና በእርግጥ አግባብ ነውን ? እነዚህ ሰዎች ስለቤተ-ክርስቲያኒቱ ጉዳይ ውሳኔ ማስተላለፍ ይገባቸዋልን ? ስለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያንስ ምን ያህል ፍቅር አላቸው ? ስለቤተ-ክርስቲያናችን ችግር ከእነዚህ ሰዎች ጋር በክብ ጠረጴዛ በመወያየት እውነተኛውን ሃይማኖት መለየት ይቻላልን ?

እኛን ተሐድሶ ይሉን ዘንድ እኛንስ ያወግዙ ዘንድ እነሱ እነማን ናቸው ? እንግዲህ ይህን በማለታቸችን ስቀለው ግደለው አስወግደው

ማለት ሳይሆን በጤናማ አእምሮ ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ብናደላ ይሻለናል እንዳሉት ዛሬም እንዲሁ ሊሆን ይገባል :: እነሱ የቤተ-ክርስቲያን ልጆች ነን እንዳሉት ከእነርሱ ይልቅ እኛ ደግሞ ነን አንዳችም የምንነቀፍበት ነገር የለንም አይኖረንምም ::

ማጠቃለያ :- ይህን ሁሉ እናገር ዘንድ ያስገደደኝ የእነርሱን ኃጢአት በመናገሬ እንደ ጽድቅ ቆጥሬው አይደለም እኔ እንደ ተንገላታሁ ይንገላቱ በማለትም አይደለም ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆቿንና ጠላቶቿን ለይታ ባለማምቅ ወደ ሞት አፍንጫ እየተጠጋች ስለሆነ ለመታደግና ምእመናንም በባለቤትነት ተወያይተውበት ታላቅ ጉባዔ ተሠርቶ አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ ገጽታ እንዲፈተሽ ተፈትሾም ነውር የሆነው ሁሉ ከውስጧ እንዲወገድ የውስጥ መናፍቃንም እንዲገሰጹ ንሥሓም እንዲገቡ ለማድረግ ብቻ ነው ::

ወገኖች ሆይ ክርስትና በዝምድና በጓደኝነት በይሉኝታ በቸልተኝነት የሚተው ጉዳይ አይደለም ምንም እንኳ ቅድሚያ የሚሰጠው ለሊቃውንት ቢሆንም ሊቃውንቱ ዝም ካሉ ግን ወይም በጥንቃቄ ካልመረመሩት ማንነታቸው አስጊ ነውና ጓዳቸው ሊፈተሽ ይገባል :: ዛሬ ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችንን ካዳከማትና ካጠቃት በሽታ ዋናው የጳጳሳት እምነት አንድ አለመሆን ነው በየዓመቱ ስለ ዓመታዊ ባጀትና የደሞዝ እስኬል እንጂ ስለ ነገረ ሃይማኖት የተወያዩበት ጊዜ የለም :: ይኸም የሚያወያይ ጉዳይ ጠፍቶ ሳይሆን እርስ በእርሳቸው ስለማይስማሙ ብቻ ነው ::

ለምሳሌም አንዱ ዘጠኝ መለኮት አማኝ ሲሆን አንዱ ደግሞ ካቶሊካዊ ነው :: አንዱም ተሐድሶ ይባላል :: ሌላውም ጨርሶ እግዚአብሔር የለሽ ነው :: ደግሞ ሁሉም ጳጳሳት በጾም ዓሣ ይበላሉ በዓውደ ምህረት ላይ ግን ዓሣ ይጾማል እየተባለ ይሰበካል :: ታዲያ እነዚህ ሰዎች በአንድ ላይ ሆነው ምን ዓይነት ውሳኔ ሊወስኑ ይችላሉ ? ስለ መናኸሳቱ የኑፋቄ ትምህርት እንኳ ማኅበረ ቅዱሳን ዕረፍት ስለ ነሳቸው እንጂ ከልባቸው አላወገዙትም ማለት ይቻላል :: የእኛ ጉዳይ ግን

የግል ጋዜጣም እንደሚከተለው ሐቁን አውጥቶታል :: እንዲያውም አንዳንዶቹ « ወንጌል ሰምቶ የማያውቀው ሲኖዶስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌል ተሰበከለት » ሲሉ ተሰምተዋል :: ጋዜጣው ግን እንዲህ ብሏል :-

## ተሐድሶ የተባሉ መምህራን
## <u>ኦርቶዶክስ ሆነው ተገኙ</u>

ከወራት በፊት ተሐድሶዎች (መናፍቃን) መሆናቸውን በማረጋገጥ "ሐመር" እና "ሰምዓ ጽድቅ" በተባሉ መጽሔትና ጋዜጣ የተወገዙት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ሠራተኞች ፍጹም ኦርቶዶክሶች ሆነው መገኘታቸው ተረጋገጠ።

በወቅቱ በተለያዩ ሚዲያዎች ተሐድሶነታቸው ሲገለጥ ቢቆይም ነገሩ እውነታ የሌለው በግል በቀልና ጥላቻ የተነሣ መሆኑን ውስጥ አዋቂዎች አመልክተው ባለፈው ሳምንት በተካሄደው የቅዳሴ ሲኖዶስ ጉባኤ ጉዳያቸው ተመርምሮ እውነታነት የሌለው በመሆኑ ነጻ መውጣታቸውን ውስጥ አዋቂዎች ገልጠዋል።

ሪፖርተራችን አንዳንድ ሰዎችን በማነጋገር እንደዘገበው ከሆነ "ተሐድሶ" የተባሉት ወገኖች ደመወዛቸው እንዲታገድና ከሥራም እስከ መገለል ተዳርገው ለወራት በመንላላት በተለይም በሊቃውንት ጉባኤው በኩል ማጣራት ሲካሄድ ቆይቶ በሊቃውንት ጉባኤውም ሆነ በሲኖዶሱ በኩል የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆች መሆናቸው የመረጋገጡ ነገር ለብዙዎቹ የቤተክርስቲያን ልጆች ኩራት መሆኑ ተሰምሮበታል።

የስም ማጥፋት ጥላሸት ተቀብተው ከነበሩት መካከል
ዲያቆን ግርማ በቀለ የሰዋስወ-ብርሃን ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የሐዲስ ኪዳን መምህር

- አባ ገሪማ ተስፋዬ በወሎ ክፍለ ሀገር ሰባኬ ወንጌል
- ዲያቆን ጽጌ ስጦታው የጉፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ሰባኬ ወንጌል
- ዲያቆን ልዑለ ቃል አካሉ በገርጂ ጊዮርጊስ ሰባኬ ወንጌል

እና ሌሎችም እንደሚገኙበት ሁሉም ወደ ሥራ ተመልሰው ያመወዛቸውን እያገኙ ቤተክርስቲያናቸውን እንዲያገለግሉና ለወንጌል አገልግሎቱም በበለጠ እንዲበረታቱ መወሰኑን ምንጮቹ ገልጠዋል። እስከአሁን "ተሐድሶ" በሚል ስለተሰራጨው የተሣሣተ ዜናም የቤተ ክርስቲያኗ ልማን በሆነው "ዜና ቤተ ክርስቲያን ማስተባበያው እንደሚሰራጭ እየተጠበቀ ነው። ታዛቢዎቹ እንደሚሉት ግን ቤተክርስቲያኗ እነዚህን እውቅ ሰባክያን ወንጌል ብታጣ ኑሮ ጉዳቱ የሃይማኖቷ ቁም*ር እንደ ነበር አውስተው የመመለሳቸው ነገር እጅግ አስደሳች ነው ብለውታል።

እነዚህን ሰባክያን ወንጌል "ማኅበረ ቅዱሳን" የተባለው ማኅበር በእኛ ማኅበር ውስጥ መታቀፍ አለባችሁ የሚሉ ጥያቄዎችን አቅርቦ መምህራኑ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሆን ብለው በሃይማኖት በማሳበብ ተሐድሶዎች (መናፍቃን) የሚል የጥላቻ ስም መንዛታቸውን ነው በቅርቡ የሚያውቁት ወገኖች የሚገልጡት።

(ዓርብ ሐምሌ 24 ቀን 1990 ልዩ እትም ፊያሜታ)

በዚህ ጊዜ ትምህርቱም ቀኖናውም ይቅር ግን አሁን ወደ ሥራው ብንልከው የከሰሱት ይገድሉታል፡ ስለዚህ እንዲያው ለማስመሰል አንድ ወር ከአምስት ጳጳሳት ጋር ለአንድ ወር ደግሞ ከአንድ ከታወቁ መምህር ቆይቶ ወደ ሥራው ተመለሰ ይባል። ይህ ካልሆነ ግን ለእኛም ጥሩ አይደለም ለእርሱም ቢሆን ሕዝቡ ስለተቆጣ አይተዉትም ተባለ። በዚህ ነገር ቅዱስነታቸው ተሸነፉ እኔ ግን

ከተሳሳትሁ አውግዙኝ እንጂ ንሥሐም ትምህርትም አልፈልግም፣ መቼ ተሳሳትሁና በማለት አቋም ወሰድሁ።

ይህን ሐሳብ የፈጠሩት ጳጳሳት የማኅበረ ቅዱሳን አባላትና ደጋፊዎች ስለሆኑ ማኅበረ ቅዱሳን ያሰራጨው ዘገባ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዳያጣ እኔም እንደተሳሳትሁ እንድመስል ነበር ። ጳጳሳቱ በትክክል ስለ እኔ ማንነት ተረድተዋል አውቀዋልም ማውገዝ የማይሞከር የማይታሰብ ነገር ነው ። በእርግጥ የእኔ መወገዝ የሚያስከትለው ነገር አልገባቸውምና ብወገዝ አንድ መናፍቅ አወገዝን በማለት ከከሳሼ ቡድን ጋር የደስታ በዓል ሊያከብሩ ነበር

በዚህ ጊዜ አቡነ ገብርኤል፣ አቡነ ዘካርያስ፣ አቡነ ናትናኤል ተመርጠው ለብቻዬ መምከር ጀመሩ። በግድ እጁን ይዘው የማልፈልገውን ማመልከቻ እንድጽፍ አስገደዱኝ። መጀመሪያ ላይ የጻፍኩት ደብዳቤ በውስጡ " በስብሰባው ላይ የተነሱት ጥያቄዎች እንደተጠበቁ ሆነው አሁን ቅዱስ ሲኖዶስ በሚለው ሐሳብ ተስማምቼ ይቅርታ ለጠይቃለኑ » የሚል ኃይለ ቃል ነበረበት። ይህንም በግድ እጁን ይዘው በሌላ ቃል እንድተካው አደረጉኝ። እሱም እንዲያው ከወረቀቱ ላይ ይስፈር ማለታችን እንጂ የልብህን እኮ አናስቀይርህም በማለት አባበሉኝ።

በእርግጥም የብዙዎች ጳጳሳት እምነት የተለያየ ነበርና እኔንም እንደነሱ እሆን ዘንድ አባበሉኝ ከእውጩ ዓለም ተምረው የመጡት ተራማጆችና ማኅበራዊ ኑሮ የገባቸው ናቸው ። በሀገር ውስጥ የተማሩት ደግሞ ጥሬና ብስል ሆነው ያሉ ሲሆኑ አንዳንዶቹ በእውቀት የተሞሉ የቤተ ክርስቲያን ነገር ግድ የሚላቸው ናቸው ። አንዳንዶቹ ደግሞ ምንም ይሁን ምን የሆነውና የሚሆነው ሲሆን ያለው የማይገባቸው መጻጸስ ፣መልበስ፣ መከበር ብቻ የሚታያቸው ናቸው ።

እኔም እሺ በማለት ከሐሳባቸው ጋር ከተስማማሁ በኋላ የሚቀጥለው መልእክት ተነገረኝ በነገራችን ላይ ከእኔ ጋር አብሮ የተከሰሰ ሌላ ሰው ስለነበር ሁሉታችንን አብረው አቀረቡን። እስካሁን ድረስ ግን ለየብቻ ነበር ሲመረምሩን የነበረው ።

የተሰጠን መመሪያም

- ✓ አቡነ አብርሃም
- ✓ አቡነ መቃርዮስ
- ✓ አቡነ ዘካርያስ
- ✓ አቡነ ገብርኤል
- ✓ አቡነ ቄርሎስ

ከሚባሉ ጳጳሳት ጋር ሐምሌን ወር በሙሉ ጥያቄ እየጠየቅን ያልገባንን ነገር እየተረዳን እንድንቆይ ተወሰነ ። ነሐሴ ወር ግን የሱባዔ ጊዜ ስለሆነ የት ብትቆዩ ይሻላችኋል? ተብለን ተጠየቅን። እኛም እንደበጉ ነገር ስለቆጠርነው ከከተማ ዘወር ለማለት ስለፈለግን ደብረ ሊባኖስ ከመምህር ገብረ ሕይወት በማለት መረጥን ። እነሱም ደስ አላቸውና በዚሁ ተወስኖአል ብለው ተስማምተው መስከረም አንድ ቀን በሥራ ገበታችን ልንገባ ተቆረጠልን ።

እኛም ሐምሌን በተመደቡልን ጳጳሳት ቤት እየተገኘን ጥፋታችን ምንድን ነው? በማለት መጠየቅ ጀመርን። እነሱም ምንም እኮ አልተሳሳታችሁም እንዲያው እኛ ለመናገር ያልደፈርነውን ነገር ተናግራችሁ ለእኛም ፈተና አመጣችሁብን ብለን ነው እንጂ ይሉን ጀመር። እንዲህ እንዲህ እያለ ነሐሴ ሲደርስ ለጸባቴው አንድ ደብዳቤ ለመምህር ገብረ ሕይወት አንድ ደብዳቤ ተጽፎ ሐምሌ 30 ቀን ከገዳሙ ገባን።

ነገሩን ሁሉ ለመምህር ገብረሕይወት አስረዳን እርሳቸው ግን አይ ልጆቼ እናንተስ ታስተምሩኛላችሁ እንጂ መቼ እናንተን ለማስተማር በቃሁ እናንተስ ተምራችኋል አሉን። እርሳቸው ተክልዬ የተቆረጡት በጦርነት እንጂ በቀዊም ወይም በጸም በጸሎት አይደለም ብለው ስለተናገሩ በገዳሙ የተጠሉ ነበሩ። በብዙ ነገር ተስማማን በሁሉም ተግባባን በጣም ደስ አላቸው። በነዚያ ቀናት ከለማይ ወረደ በተባለው መስቀል ጀርባችንን ሆዳችንን ሰውነታችንን እየታሸን ሰነበትን ::

# ደብረ ሊባኖስ ገዳምና የደረሰብን ድብደባ

ከአስተዳዳሪው ከአባ ገብረ ማርያም አጽብሐ ጋርም የተነጋገርነው አለ :: አሁን አልገልጠውም ሆኖም ወቅቱ የሱባዔ ወቅት ነበርና ከአዲስ አበባ ለጸሙ ወደ ገዳም የመጡት የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ከቤተ-መቅደሱ ፊት ለፊት ከቅኔ ማኅሌቱ ላይ ሲመለከቱን ባንዴት ጥርሳቸውን አፋጩ፣ ወዲያውኑ ለመነኮሳቱ ሁሉ እየዞሩ የተክልዬ እግር የተቆረጠው በጦርነት ነው ያለው መናፍቅ መጣላችሁ ኑ እንግደለው በማለት አወኩት :: ያኔ መነኮሳቱ ሁሉ መውጊያ አይሉት መባረኪያ በትረ-መስቀሉን እየመዘዘ አካባቢውን በጠበጠው :: አውጡና ስጡን እንረዳቸው፣ እንብላቸው ይባባል ነበር :: እኛም ነፍሳችን ተጨነቀች በትክክልም ከእጃቸው እንተርፋለን የሚል እምነት አልነበረንም ::

አባ ገብረ-ማርያም ዚችም ግን ከጳጳሳት ማረፊያ ቤት ካስገቡን በኋላ ስለእኛ ሲከራከሩ ዋሉ :: አይደለም ሲኖዶሱ ነው የላካቸው አርፋችሁ ጸማችሁን ጹሙ ቢሉም ሲኖዶስ ማን ነው ? ሁሉንም እናውቀዋለን :: አንፈልግም ይልቅስ ያውጡልን በማለት ይደነፉ ጀመር :: ነገሩ የማይቻል ሲሆን ነሐሴ 3 ቀን ከገዳሙ እንድንወጣ ተወሰነ።

ዕለቱ እሑድ ነበር። ሁለት የጥበቃ ጓዶች ተመደቡልን፣ ለካ መነኮሳቱና ማኅበረ ቅዱሳን እሑድ ሧት ውሻ ገደል ከተባለ ጫካ ውስጥ ተደብቀው ለመግደል ተስማምተዋል ።

ይህን ምሥጢር የጥበቃ ክፍሎችም አውቀውት ተባብረው ኖሮ ፣ በጥሩ ሁኔታ አመቻችተዋል ። እኛም በግምት 11:30 አካባቢ ውሻ ገደል ስንደርስ እልፍ አእላፍ ሕዝብ ድንጋይ፣ ቆመጥ፣ ገጠራ፣ ብረታ ብረት ይዞ ከበበን ዓላማቸው እኛን በመግደል በረከት ማግኘት ስለነበር፣ ለሕይወታችን አልሳሱላትም ነበር ። ጨካኞች አረመኔዎችና ክፉዎች ናቸው እንምከር እናስተምር የሚባል ነገር ከልባቸው የለም መልካም ነገር ከእነርሱ ዘንድ ተወስዷል ። ምነው ተክለ ሃይማኖት እንኳ ሰይጣንን ያህል ጠላት ይቅር ብለው ታርቀው አስተምረው ገነት መንግሥተ ሰማያት አስገብተው አልነበረምን ? ይህን ደግነት ከተክልየ አይማሩትምን ?

ሁሉም ተነክልዬን ለማስደሰት የያዘውን ብረት፣ ድንጋይ ወዘተ በላያችን ላይ አፈሰሰው እኔም ደም አስከሮኝ ወደቅሁ በእኔ፣ በሞት መካከል አንድ እርምጃ ያህል ቀርቶ ነበር። ሁሉን ነገር አላውቅም ነበር ። መከራው የደረሰብኝ ጭንቅላቴ እስኪሰባበር ድረስ ነበርና ከብዙ ድብደባ በኋላ ግን ራሴን አላውቀውም ነበር በሕይወት መትረፌ ለከሳሾች ጥሩ ስላልነበረ ጨርሰው የገደሉኝ መስሏቸው ነበር ። ለእኔም ነእነሱም ተአምር የሆነብን ያ ሁሉ መዓት ወርዶብኝ ዛሬ በሕይወት መገኜቴ ብቻ ነው ።

በእርግጥ እግዚአብሔር በእኔ ላይ ዓላማ እንዳለው ተረዳሁ ማኅበረ ቅዱሳን ግን ለምን ይህን ክፋት ፈጸማችሁ ? ተብለው ሲጠየቁ « የመናፍቃን ትራክት ሲበትኑ ተገኝተው ነው » ብለዋል ። ግን « በሕያው ስሙ ደፍሬ እምላለሁ » በሕይወት ዘመኔ የጴንጤ ትራክት በትኜ አሰራጭቼ አላውቅም እኔም ሆንሁ አብሮኝ የነበረው ጓደኛየ ይህን ሥራ

ሞክረነው አናውቅም ክፉዎፍ አመጻቸውን ይፈጽሙ ዘንድ እንዲህ ዋሹብን እንጂ ::

አሁንም እንኳ ይዋሻሉ አባት አጣን እንጂ ቢኖረንማ በግንባር አንወያይበትምን ? ግን የፈጸሙት በደል ፊት ለፊት የሚያስቆም ስላልሆነ በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ መወያየትን አይወዱም እነርሱ ገድለውኛል እኔም በእነርሱ ዘንድ የሞትሁ ነኝ በክርስቶስ ግን አሁን ሕያው ሆኜ እኖራለሁ :: እነርሱማ ገደልነው ብለው ስለሞትሁላቸው ጥለውኝ ሸሹ ጓደኛዬ ግን ብዙ አልተጐዳም ነበርና እኔን አፋፍሶ ጤና ጣቢያ ሲወስደኝ ቶሌ አዲስ አበባ ካልደረሰ ደም ወደ ውስጥ ፈሶ ይሆናልና ይሞታል አለ :: በዚህ ጊዜ እንደምንም በተገኘው ትራንስፖርት አፋፍሶ አዲስ አበባ ቅዱስ ገብርኤል ከፍተኛ ክሊኒክ (አልተርኔት) ከሦስት ቦታ ላይ ጭንቅላቴ ተሰፍቶ አእምሮዬን ሳላውቅ ሰነበትሁ በዚህ ጊዜ አንድ ስሕተት ተፈጠረ ::

ጓደኛየ በደረሰብን አደጋ ስለተበሳጨ ወዲያውኑ ማመልከቻ በእርሱና በለኔ ስም ጽፎ እውር ድንብሬን ካስፈረመኝ በኋላ ደብዳቤው በወቅቱ ሥራ አስኪያጅ ለነበሩት በቅርብ ለማውቃቸው አባት ለአቡነ ቄርሎስ ሰጣቸው :: የደብዳቤው ፍሬ ሃሣብ "እኛ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት ቅድስት ቤተክርስቲያናችንን ለማገልገል ታጭኛ እንደሆንና ነገር ግን ማኅበረ ቅዱሳን ሊያሠራን ስላልቻለ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለመልቀቅ ተገደናል" ይል ነበር ::

እኔም ዓይኔ ተደፍኖ ማየትም መስማትም አልችልም ነበርና ስለጻፈው ደብዳቤ ሲነግረኝ በጣም ተበሳጨሁ :: ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ሲሻለኝ የራሴን ማመልከቻ ይገፍ ከአቡነ ቄርሎስ ስገባ በጣም አዘኑብኝ :: ጓደኛየ የጻፈውን ሲያሳዩኝ እኔም አዘንሁ :: ነገር ግን የሆነውን ሁሉ

አስረድቼ ሌላ ማመልከቻ እንድጽፍ አዘዙኝ እኔም እስካሁን ያላለቀለትን ማመልከቻ ይዤ ገባሁ ምልክት አድርገው ለልዩ ሲኖዶስ መሩት እስከአሁን አልተፈጸመልኝም ። እኔም ደጅ ጥናቱን አልተውሁም ። አሁንም ቢሆን ይህን መጽሐፌን ይዤ ደጅ እጠናለሁ እኔም ሆንሁ መሰል ጓደኞቼ በቅዱስ ሲኖዶስ ፊትና በሊቃውንት ጉባዔው ፊት በአደባባይ መወያየት እንወዳለን እንፈልጋለንም ።

# የችግሩ መንሳኤና ፈጣሪ ማን ነበር ?

ለዚህ ሁሉ ፈተና ያጋለጠኝ ማን ነው? ማኅበረ ቅዱሳን አይደለምን? በእርግጥ ጥፋት ነበረብኝን? እንግዲህ ሊቃውንት ጉባዓ ውም፣ ቅዱስ ሲኖዶሱም መረመረኝ አንዲት ስንኳ በደል አልተገኘብኝም። ነገር ግን ይህ ማኅበር ስቀለው ስቀለው አስወግደው በማለት ከምወደው አገልግሎቴና ከሕዝቤ ለየኝ። ለመሆኑ ይህ ማኅበር ማን ነው? እንዴት እንደተጀመረ፣ እንዴት ከዚህ እንደደረሰ፣ ምን ምን ሙስናዎች ፈጸመ የሚሉትን ከዝዋይና ከናዝሬት ጀምሮ እስከ አዲስ አበባ የየግል ሕይወታቸውና ማንነታቸውን በመጽሔታቸው የፈጠሩት ስሕተት ምን እንደሚመስል ከበቂ መረጃ ጋር አዘጋጅተነዋልና እነሆ።

ምንም እንኳ የልጆቹን ጉዳይ የመረመረው ሲኖዶስ ትክክለኛ የቤተ-ክርስቲያን ልጆች እንደሆኑ አምኖ ወደ ሥራቸው ለመመለስ ቢወስንም በጥቅምና በዘረኝነት የታሠሩ ጥቂት ጳጳሳት አጉረምርመው ነበር። ማጉረምረማቸው ግን ማኅበረ ቅዱሳን ከእንግዲህ ታማኝነቱን ያጣል ከማለት የተነሣ እንጂ ሌላ ምንም አልነበረም። ማኅበረ ቅዱሳን ግን የሊቃውንቱ እንደገና ወደ ቤተ-ክርስቲያን መመለሳቸው ጥፋታችንን ያፋጥጉታል ከሚል ስጋት የተነሣ ግማሾቹን ገደለ፣ ግማሾቹን ደበደበ፣ ግማሾቹን አሳደደ።

በአሁኑ ሰዓት በገንዘብ ኃይል የሚንቀሳቀሰው ይህ ፀረ ወንጌል ማኅበር እውቅ ሰባክያንን ስማቸውን በመጥቀስ አገልግሎታቸውን ለማሰር ቢሞክርም ነፍስን እንደመጉሰም ሆነበት እንጂ ሌላ ያተረፈው ነገር የለም። ማኅበረ-ቅዱሳን ከስም በስተቀር ምንም መንፈሳዊ ሕይወት የሌለው ሲጀመር ጀምሮ በዝሙትና በዛር መንፈስ የተመሠረተ የአጋንንትን ትምህርት የሚያስተምር፣ የዲያብሎስ ደቀ መዝሙር ነው።

እንግዲህ ማኅበረ ቅዱሳን እኔ የቤተ-ክርስቲያን ልጅ ነኝ ይል ዘንድ አፍ የሌለው ለንስሐም ያልታደለ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ከማጣመም ያልተቆጠበ፣ በገንዘብ የሰከረ ምድራዊ ብቻ ድርጅት ነው። በአሁኑ ሰዓት የቤተ-ክርስቲያንን ሥልጣን ሊቀማ የቋመጠው ይህ ማኅበር ለጊዜው ብቻ የተለሳለሰ ሕይወት ያለው መምሰሉ ለየዋሑ ሕዝብ ግልጽ አልሆነለትም።

የቤተ-ክስቲያኒቱን ቋንቋ ፈጽሞ የማያውቀው ይህ ማኅበር የፈለገውን ያህል ቢዝትም ካለበት የተግማማ የሕይወት ታሪክ የተነሣ አንገቱን ይደፋል እንጂ ተቃንቶ ሊራመድ አይችልም። ሌባ ማንነቱን በሚያውቁት አካባቢ ሲያልፍ ተከናንቦ አሊያም አንገቱን ደፍቶ ያልፋል። ማኅበረ ቅዱሳንም ይህ ገመናው እስኪገለጥ ድረስ እንጂ ያኔ አንገቱን ይደፋል። እንግዲህ በመጀመሪያው ላይ የጠቆምናቸውን ነጥቦች በዝርዝር ከበቂ ማብራሪያ ጋር ይዘን ለሕዝብ ማነቃቂያ ትሆን ዘንድ ይህችን መጽሐፍ አበርክተናል ::

እንግዲህ ስለነሱ ዝም አንልም በጠማማ ትምህርታቸው የወጥትንም ሕዝባችንን እንደገና በክርስቶስ ወንጌል እንደ ቤተ-ክርስቲያናችን አስተምህሮ እያቀረብን እንፈውሳለን። ለዚህ ማኅበር ያልሰገደና ያልተገዛ ሁሉ እንደከሐዲ የሚቆጠርበት ይህ ማኅበር

ያወገዛቸው እነማን እንደሆኑና በምን ምክንያት እንዳወገዛቸው በዝርዝር ስናቀርብ ማኅበረ ቅዱሳን በራሱ ውግዘት ራሱ ተወግዞ የሚለይ መሆኑንም በእርግጠኝነት እንመሰክራለን። ምንም እንኳ በአሁኑ ሰዓት በሥልጣን ላይ ያለው ቅዱስ ሲኖዶስ ብቻ የቆመ ቢመስልም ከእናንተ ይልቅ ለእግዚአብሔር ብንታዘዝ ይሻላል የሚል ልዩ እረኛ እግዚአብሔር አስነሥቷልና።

ነገርን ሁሉ ለአባቶች ማለትን ትተን ትክክለኛዋንና ቀጥተኛዋን አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደገና ለማቆም ተነሥተናል ።

ከእንግዲህ ለክፉዎች ምህረት አይኖረንም ። ምንደኛም የቤተ-ክርስቲያን ጠባቂ ሊሆን አይችልም "አሥግሩ ለነ ቁናጽለ ንዑሣነ እለ ያማስኑ አፀደ ወይንነ" የወይን ቦታችንን የሚያጠፉትን ጥቃቅን ቀበሮዎች አጥምዳችሁ ያዙልን እንደተባለ ቀበሮው ማኅበረ ቅዱሳን ከእንግዲህ በቤተ-ክርስቲያን እድሜ የለውም። ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ እንዲህና እንዲያ እያለ የሚናገረው ይህ ማኅበር ራሱን እንዳያውቅ የሊቃውንት መድረክ እነሆ ተከፈተ። ዝም ማለታችንን ወደ ፕሮቴስታንት ጉራ እንደተቀላቀልን የቆጠረው ይህ አስመሳይ ማኅበር የትና በምን ሁኔታ እንዳለን አሁን በግልጥ ይረዳ ዘንድ ተገልጠንለታል። ከማኅበረ ቅዱሳን ጀምሮ ማናቸውም ልዩ ወንጌልን የሚሰብክና ሊመሰገን የሚገባውን የማያመሰግን፣ ሊዘመርለት የሚገባውን የማይዘምርለት፣ እርሱን እርቃኑን ለመግፈፍና ሐፍረቱን ከማሳየት ወደ ኋላ ላንል ተነሥተናል።

ማኅበረ ቅዱሳን ነኝ ያለው ይህ ማኅበር በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር እገሌ ብሎ ስም የሚጠራበት አንደበት እስከማይኖረው ድረስ ማንነቱን ለምዕመናን ልንገልጥ ቃል እንገባለን "ለቤተ

ክርስቲያኒቱ ከኔ ወዲያ ለሃሳር" ብሎ የተነሣው ይህ ማኅበር "ለቤተ ክርስቲያኒቱ ከእኔ ወዲያ ማፈሪያ ለሐሳር" የሚልበት ቀንም ቅርብ ነው። ራሱን አጽድቆ እገሌ ኃጥዕ፣ እገሌ መናፍቅ በማለት ራሱን የሾመው ይህ ማኅበር ማንነቱ ሊታይ እርቃኑ ሊገለጥ ጊዜው አሁን ሆኗል። ሕዝባችን በየተራራውና በየኮረብታው እንዲንበረከክ፣ አምልኮ ባዕድን እየተከተለ እንዲያመነዝር፣ በማድረግ እንደ ምናሴና እንደ አመንዝራይቱ እንደ ኤልዛቤል ከፍተኛ ሚና ያለው ይህ ማኅበር ሊጠፋ እግዚአብሔር የበቀለ ሰይፍ አንሥቶበታል።

ቢጽ ሐሳውያን ሐዋርያትን እግር በእግር እየተከተሉ ጥምቀት ያለ ግዝረት፣ ወንጌል ያለ አሪት፣ ክርስቶስ ያለ ሙሴ ሊያጸድቋችሁ አይችሉም እያሉ እንግዳ ትምህርትን እያስገቡ ሐዋርያትን እንዳወኩ ሁሉ ዛሬም የቢጽ ሐሳውያን ደቀ መዛሙርት ሐዋርያቱን እየተከተሉ በጥፋ ትምህርታቸው የሕዝብን ልብ ለማጣመም ሞክረዋል ። ሆኖም የማይችሉት የወንጌል እሳት ስለተቀጣጠለ ሊያጠፉት አይችሉም።

ከእንግዲህ "ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ከአንተ ጋር ምን አለን ያለ ጊዜያችን ልታጠፋን መጣህን ብትፈቅድስ ወደ አሪያዎች መንጋ እንድንሄድ እዘዝ" እንዳሉት ይህንም ማኅበር የሚጠብቀው ይኸው ነው። ይህ ማኅበር ሊቃውንቱን "ሲሞን መሠርይ" ሲል ኮነነ እንጂ በጥቅም ታውሮ በክፉ መንፈስ ተበክሎ ክርስቶስን ሳይሆን የራሱን ትምህርት የሚሰብክ ትክክለኛ ሲሞን ራሱ ማኅበረ ቅዱሳን ነው። ማኅበረ ቅዱሳን እንደ ሐገር ውስጡ መስሎት በውጭ መድረክ ሊቆምና የተለመደ ኑፋቄውንና ፖለቲካውን ለማናፈስ ቢሞክርም አፍሮና ተዋርዶ ቅሌቱን ተከናንቦ መመለሱ እንደ አኪሖፈል በራሱ እጅ ታንቆ የሞተን ያህል ቆጥሮታል።

ሐቁ ይነገር ከተባለ የአሜሪካው ሲኖዶስ እውነተኛ የወንጌል ልጆችን እየተቀበለ በተገቢው ቦታ ማስቀመጡ እነ ይሁዳን እያስወጣ እነ ማትያስን መተካቱ ግዴታውንና ተልዕኮውን የተወጣ መሆኑን በግልጽ ያሳያል ። "የአዲስ አበባው መናፍቅ የአሜሪካው ቄስ" ብለዋል። በአዲስ አበባ ከተማ ኦሪት እንጂ ወንጌል ስለማትሰበክበት የአይሁድና የሰዱቃውያን ቤተ-መቅደስ ሆናለች በዚህም ሐዋርያትና ክርስቶስ መሰበክ ባልቻሉ ጊዜ ይድኑ ዘንድ ወደአላቸው ዘወር ብለዋል ።

"የአዲስ አበባዎች ቄስ የአሜሪካዎች መናፍቅ" ደግሞ እናንተ ናችሁ። እነብርሃኑ ጉበና ወደ አሜሪካ ብቅ ብለው ለመወያየት ሞክረው ስለአላማቸው ሲገልጡ "እኛ ግንኙነታችን ከእናንተ ጋር እንጂ ከአቡነ ጳውሎስ ጋር አይደለም ስለዚህም አብረን እንሥራ" ብለው ነበር። ግን ታላቁ ሊቅ የወንጌል ዝሪፊ ቢጸ ሐዋርያት ሲመልሱ "እናንተ የእፉኝት ልጆች መጀመሪያ ንሥሐ ግቡ አሁን ውጣልኝ ሥራዬን ልሥራበት" ተብሎ ተዋርዶና አፍሮ ተመልሷል። ይህን ቁጭት ለመወጣት ሲባል "መናፍቅን የሚቀበል ራሱ... " የተባለው ብርሃኑ ጉበናን ቢቀበሉት ኖሮ ብዙዕነታቸው ትክክለኛ ኦርቶዶክስ ይሆኑ ነበር ማለት ይሆን ? ።

ማኅበረ ቅዱሳን በአሜሪካስ አይሳካለትም፣ ይልቅስ የያዘውንም እንዳያጣ ሕያው እንደመሆኗ ስም ያላት ነገር ግን የሞተችውን የአዲስ አበባይቱን ቤተ-ክርስቲያን እየቀበረ ተዝካሯን እያወጣ ቢበላ ይመረጣል።

ዶሮ ጭራ ጭራ ታወጣለች ካራ

ለሰውም አይደለም ለራሷ መከራ

ተብሎ እንደተነገረው ይህ ማኅበር ነገር ጭሮ ጭሮ ለራሱ መታረጃ ካራን አውጥቷል። እንግዲህ ነገር ተጀመረ፣ ክብሪት ተጫረ፣ እሳት ተቀጣጠለ፣ የሚያፍርም ሊያፍር፣ የሚከብር ሊከብር፣ የሚቃጠል

አመድ ሊሆን፣ የማይቃጠል ነጥሮ ሊወጣ "ሀ" ተብሎ ተጀመረ። በውስጡ አንድም የቤተ-ክርስቲያን ዲያቆን የማይገኝበት ነገር ግን እንደ ካህናተ ጣዖት እርስ በእርሱ እየተሿሿመ የሚፋጉንበት ይህ ማኅበር ራሱን የሚያጣበት ቀን ዛሬ ነውና ሕዝባችን ሆይ ራስህን አድን ።

ወደ ኋላህ አትይ ማኅበረ ቅዱሳን ይወድቃል። በአጠገቡ የሚያልፉ ሁሉ በፉጨት እያንጉራጉሩ በእርግጥ ያ ግዙፍ ማኅበር እንዲህ ወደቀን? ይላሉ ። ከእንግዲህ ይህ ማኅበር ያለነውርና ያለነቀፋ በነበረች ቤተ-ክርስቲያናችን ውስጥ ሽባ የሆነውን ትምህርቱን አያካሄድም ። ከዚህ የበለጠ ጥፋት ሳያደርስ ይበቃል ልንለው ነው ።

ማኅበረ ቅዱሳን ማን ነው ?
እንዴት ተጀመረ ?
ማን ጀመረው ?
መቼ ተጀመረ ?
ባለዛሯ የት ደረሰች ምንስ ትሠራ ነበር ?
12ቱ ደናግሉች ምን ተደረጉ ?
ለራዲዮ የሰጡት ቃለ ምልልስ ምን ይላል ?
ስዩም ያሚና ግርማ በቀለ ለምን ተለዩ ?

ከነሻምበል ግዛው ዳኛው ጋርስ በራዲዮ እንዴት ተነጋገሩ የሰጡት ምሥክርነትስ ? የሚሉትና ሌሎችም ሁሉ በእጃችን ስለገቡ አእምሮ የተባለው የግል ጋዜጣ በዚሁ ዙሪያ ተከታትሉ የታዘበውን አካተን በመጽሐፍ መልክ ስላዘጋጀን ሕዝባችን ከዚህ ማኅበር ፈቀቅ ይል ዘንድ ሐቁን መልእክታችን እናስተላልፋለን።

ቦ ጊዜ ለኩሉ
ለሁሉም ጊዜ አለው

# ክፍል ሦስት

## እኛም ስለ እነርሱ እንናገር

### ማኅበረ ቅዱሳን ማን ነው?

### እንዴት ተጀመረ ?

### ማን ጀመረው ?

እውን ማኅበረ ቅዱሳን ብላቴን ላይ የተመሠረተ ማኅበር ነውን? ስለ እኛ ብዙ ጽፈዋል፣ ብዙም ተናግረዋል። ምንም የቀረ የተሠወረ ነገር የለም። ከእውነት የራቀውና በሐሰት የተቀነባበረው እውቀትም የጐደለው እምነታቸው በንግግራቸውና በጽሑፋቸው ተገልጧል። አየንም፣ ሰማንም፣ ማንነታቸው ይህ ከሆነ እኛም ስለነእርሱ እንዳየንና እንደሰማን ከመሉ የድምጽና የጽሑፍ ማስረጃ ጋር አገር ያወቀውን፣ ዐሐይ የሞቀውን ታሪካቸውን እንናገራለን።

ማኅበረ ቅዱሳን ብላቴን ላይ ተመሠረትሁ አለ እንጂ ከብላቴን በስተጀርባ ሌላ ስውር ድራማ አለ። የሰው ምሥክር እንኳ አያስፈልገንም ማኅበረ ቅዱሳን ከዝዋይ እስከ ናዝሬት ከናዝሬት እስከ አዲስ አበባ፣ ከአዲስ አበባ እስከ ብላቴን ከዚያም እስከ አሁን ያለውን ማፈሪያ ታሪኩን "ሀ" ብለን ጀምረናል።

ስም ማጥፋት ይመስልብልናል ብለን ነበር መንግሥታዊ መረጃዎች እንኳ እንደ ምሥክር ስለሚሆኑን እነሱን በእጃችን ካስገባን

በኋላ ጉዳዩን ለሕዝብ ለማሳወቅ ወደድን።ከመሠረቱም ቢሆን ማኅበረ ቅዱሳን በዛር መንፈስ እየተመራ ሥራውን የጀመረ በመሆኑ ማኅበረ ቅዱሳን የሚለው ስም የእነሱ ሊሆን ከቶም አይገባም "መልክ ጥፉን በስም ይደግፉ"እንደሚባለው እርኩሱን ማኅበር ቅዱስ ብሉ መሠየሙ ጨለማውን ብርሃን እንደማለት ነው ። ማኅበረ ቅዱሳን ከማትሪክ ስለ ቤተ-ክርስቲያኒቱ ታሪክ ወይም ስለ ነገረ ሃይማኖቷ ጠለቅ ያለ እውቀት የሌላቸው ናቸው ።

ይህ ማኅበር ቅድስናው የተዳደፈና ቤተ-ክርስቲያናችንንም ፈጽሞ ሊወክላት የማይችል ቤተ ክርስቲያንም የማታውቀው እረኞች ተኝተው ሳሉ ጠላት የዘራው እንክርዳድ ነው ።

"ጅብ እስኪይዝ ያነክሳል" እንደሚባለው ፓትርያርክም ሆነ ቄስ ከራሱ ምልምሉች እስኪሾምና ሁሉንም እስኪወርስ ድረስ ጤናማ መስሎ መታየቱ ብዙ ሰው እንዲከተለው ሆኗል።

የተበላሸና የተሳሳተ አስተምሕሮ ያለው ይህ ማኅበር ክርስቶስን የማያውቅና ከወንጌል ክልል የወጣ፣ ተረት ተረት የሆነውንም ከንቱ ትምህርት የሚያስተምር ሆኖ ሳለ ስህተቱን፣ ድክመቱን መነሻውንም የሚያውቁትንና የቤተ-ክርስቲያን ጤናማ ልጆች የሆኑትን ቤተ-ክርስቲያንም ልጆቼ ብላ ተቀብላ ቦታ የሰጠቻቸውን ምሁራን በሊቃውንት ጉባዔም ሆነ በሲኖዶስ አንዳችም ኩሩቁ ያልተገኘባቸውን በራሱ ደካማና ሽባ በሆነው መጽሔትና ጋዜጣ በሲኖዶስ እንደተወገዙ አስመስሎ በማውጣት ደጋግሞ አስነብቧል።

«መልክ ጥፉን በስም ይደግፉ » እንደሚባለው ይህ ማኅበር ለዓላማዉ ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ሰዎች በተለያየ ጥቅም መያዝና

አካሔዱን የማይቀበሉትን ደግሞ ስም በማጥፋት እንዲጠሉና እንዲገለሉ ማድረግ ዋና ስልቱ ነው ::

## ነፍሰ ገዳዩ ማኅበር (ማኅበረ ቅዱሳን)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ሲያስተምር "ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ለሌላ አይመጣም" ብሏል (ዮሐ. 10÷10) መቼም ቢሆን ትናንትም ቢሆን ዛሬም ቢሆን ነገም ቢሆን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚለይ ማናቸውም ቡድን ነፍሰ ገዳይ ነው። ከቆምንበት ዓለት የሚያነቃንቀን "መዳን በሌላ በማንም የለም" ከተባለው ስብከት ሌላ የሚሰብከን እርሱ አጥፊና አራጅ ነው። መቼም ቢሆን ሰይጣን በራሱ ስምና ግብር ወይም በራሱ የታሪክ መጽሐፍ እያስተማረ አይገለጥም።

- ሰይጣን በብርሃን መልአክ ይመሰላል (2ቆሮ. 11÷14)፣
- ሰይጣን በቅዱሳን ሐዋርያት ይመሰላል (2ቆሮ. 11÷13)፣
- ሰይጣ፣ በክርስቶስ ስም ይመጣል (ማቴ. 24÷5)፣
- ሰይጣን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ያሳስታል (ማቴ. 4÷5)፣
- ሰይጣን ከክርስቶስ ይልቅ ለክብራችን እንድንቆም ያደርገናል (ዮሐ. 12÷42)፣
- ሰይጣን በክርስቶስ እንዳናምን ልቡናችንን ያሳውራል (2ቆሮ. 4÷4)

ቅዱስ መጽሐፍ ስለ ሰይጣን ክፋት ብዙ ይናገራል። ሰይጣን የሥላሴን ሦስትነት አንድነት የቅዱሳን መላእክትንና የጻድቃን ሰማዕታት ታሪክ አበጥረን አንጠርጥረን ብናውቅ ቅንጣት ታህል አይጨነቀውም። የሰይጣን ጭንቀቱ ከዚህ ጋር የኢየሱስ ክርስቶስን ብቸኛ አዳኝነት ማወቅና ማመን፣ በእኛ ሕይወት ውስጥ ሲከናወን ብቻ ነው። በመሆኑም እልፍ አእላፍ ታሪክ እየተረክን ከክርስቶስ አዳኝነት ራሳችንን እንድናገል በማድረግና ይህንም በማወቅ እንደ ጻድቃን

እያስመሰለን ከጸጋው ወጥተናል። ሰይጣን ይህን ከባድ አደጋ ለመፈጸም ቀኝ እጁ አድርጉ ያቆመው ይህ ማኅበር ማኅበረ ቅዱሳን ነው። ማኅበረ ቅዱሳን ለሰይጣናዊ ተልዕኮ በቅዱሳን ስም ተከናንቦ የሰይጣን መልእክተኛ በመሆን ራሱን ሳያውቀውና ሳይገባው አደራጅቷል።

ዮሐንስ ስላለንበት ስለመጨረሻው ዘመን በራእይ ሲመለከት አንድ አውሬ ከባሕር ሲወጣና ቅዱሳንን ለመውጋት ሥልጣን እንደተሰጠው ድልም ያደርግ ዘንድ እንደተፈቀደለት ብዙዎቹም አውሬውን እንደተከተሉት በአድናቆት ጽፏል (ራእይ 13÷1) ማኅበረ ቅዱሳን ከክርስቶስ ውጭ በሆነ ሕይወት እየኖረ የክርስቶስ የሆኑትን በማሳደድ በአመንዝራይቱ በኤልዛቤል መንፈስ የተሞላ ቡድን ነው።

የማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት "እግዚአብሔር ፍጹም ጨካኝ ስለሆነና ስለማይሰማን በርኅራኄ ከእርሱ የተሻሉ ቅዱሳን ጻድቃን በፊቱ ቆመው እንዲለምኑልን የነርሱ ልመና ግድ ብሎት ስለሚምረን በአማላጅነት እንመን ይላል።" ይህም የትምህርቱ ትልቁ ክፋት ነው። በክርስቶስ የማያናር ሁሉ በሞት ጥላ ሥር መሆኑን ጌታችን እየተናገረ። ይህ ጠማማና ነፍስ ገዳይ ማኅበር ግን ክርስቶስ በአምላክነቱ ከታወቀ በቂው ነው በማለት ቤዛነትንና አዳኝነትን ለድንግል ማርያምና ከእርሷ በታች ላሉ ፍጡራን አድሏቸዋል።

በተለያዩ ጽሑፎቹ የሞት መልእክትን እየበተነ ያለው ይህ ማኅበር ከአነሳሱ ጀምሮ ስለምናውቀው እስከ መጨረሻው እንቋቋመዋለን። ይህ ማኅበር ደርግ የዩኒቨርስቲ ተማሪያዎችን ወደ ብላቴን ማሰልጠኛ ከማስገባቱ በፊት ከ1982-1983 ዓመተ ምህረት ላይ ሁለትና ሦስት በመሆን ዝዋይና ናዝሬት ላይ ብቅ ጥልቅ እያሉ መሰባሰብ ጀመሩ። ይህ ጅማሬ በጥቂት ጊዜ ውስጥ በሦስት ወንዶች / ዲያቆን እሸቱ፣ ስዩም ያሚ፣ ዲያቆን ግርማ በቀለና በ10 ሴቶች

በድምሩ ወደ 13 አባላትን አሰባሰበ ከነዚህ መካከል ሁለት እጎትማማቾች ነበሩ።

ታላቋ በዛር መንፈስ የተሞላች ሆና ዛሩ ሲወርድ ሚካኤል ነኝ ወይም ማርያም ነኝ በማለት በቅዱሳን ስም ያታልላቸዋል። ከሦስቱ ወንዶች አንዱ የሆነው ለዚህ መንፈስ እንደልዩ አገልጋይና ቃል ተቀባይ በመሆን በራሱ ተነሣሽነት ለአገልግሎት ይመደባል። በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ያላደጉ ልጆችን በግላጭ ያገኘው ይህ የዛር መንፈስ ልዩ መልእክተኛ አድርጉ በመረጠውና በሾመው በዲያቆን እሸቱ በኩል የሚፈለገውን መልእክት ሁሉ ለአባላቱ ማስተላለፍ ይጀምራል።

መልእክቱ የሚመጣው በልጅቱ ላይ መንፈሱ ወርዶ ከጣላትና እየተንፈራፈረች ከቆየች ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ነው። ከዚህ ግርግር በኋላ ይህ ዲያቆን በታዛኝነት ከዛሩ የሚወጣውን ትዕዛዝ ለመቀበልና ለማስፈጸም ተዘጋጀ ይላል። እርሱም ታጥቆና እጅ ነሥቶ ይቆማል። ከዚህ በኋላ ዛሩ እኔ ማርያም ነኝ፣ ዛሬ የማገዛችሁ በዚህ በመሰብሰቢያው አዳራሽ ውስጥ ባለው መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ ብር፣ ወርቅ፣ ገንዘብ ያላችሁን ሁሉ አምጥታችሁ አስቀምጣችሁት ሂዱ በዘነጋው መጥታችሁ ስታዩት ካጣችሁት እኔ እንደተቀበልኳችሁ እወቁ ተቀምጦ ካገኛችሁት ግን በሥጦታችሁ ደስ አልተሰኘሁምና ንሥሐ ትገቡበታላችሁ ቀንሳችሁ ያስቀራችሁትም ካለ ሁሉንም አምጡ ያኔ እወስደዋለሁ የሚል መልእክት ይናገራል።

ዲያቆኑም የተባለውን ሁሉ ለሴቶቹ ያስተላልፋል፣ የሰሙትም ሴቶች ከሰሙት ቃል አንዱንም ሳያጓድሉ አንዳንዶቹ የወላጆቻቸውን በመስረቅ አንዳንዶቹ ደግሞ የራሳቸውን የባንክ ገንዘብ፣ የጆሮ፣ የአንገትና የጣት ጌጣቸውን ሁሉ በማውለቅ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በመፎካከር እያመጡ በየራሳቸው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አስቀምጠውት

ይሄዳሉ። ለጭካኔያቸው ወደር የማይገኝላቸው ዲያቆኑና ባለዛሯ ሌሊት ከመኝታቸው በመነሣት የተቀመጠላቸውን ወርቅ የገንዘብ መግት ሰብስበው ያስገባሉ።

አንሶ ካገኙት ግን መልሰው ከቦታው ያስቀምጡታል ሲነጋ ባለገንዘቦቹ መጥተው ሲያዩት የተወሰደላቸው በደስታ ይፈነድቃሉ፣ ያገኙት ግን እመቤቴ ተቀይማኝ ነው በማለት ደም እንባ እያለቀሱ ይውላሉ። ከዚህም የበለጠ እንዲያደርጉ ምክር ይሰጣቸውና እንደገና ከዚህ በላይ ሌላ ነገር ጨምረው ያመጡና ተቀባይነት እንዲያገኙ ያደርጉታል። ሴቶቹ በትክክል የእመቤታችን መልእክት ነው ብለው ያምኑ ስለነበር ነገሩን ሁሉ በጥንቃቄና በፍርሃት ያደርጉት፣ ይጠብቁትም ነበር።

ነገሩን የበለጠ እንዲፈራና እንዲታመን ያደረገው የዛሩ መልዕክተኛ ዲያቆን መሆኑ ነው። ከዚህ በኋላ ግን እነ ስዩም ያሚና ግርማ በቀለ ነገሩን በጥሞና ይከታተሉት ጀመር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከማኅበሩ ውስጥ አንዱ የነበረው ስዩም ያሚ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ አገር ሄደ። ከዚያም እያለ ልጆቹ በዚህ መንፈስ እየተመሩ መሆኑን እንደምሥራች አድርገው ቆጥረው ደብዳቤ ጻፉለት። እርሱ ግን ይህ የአጋንንት ሥራ ነው እንዳትቀበሉት ከሐሰት ትምህርት ተጠንቀቁ ብሉ ጽፎ ነበር። በጥቅምና በድንቁርና የተሞላው ዲያቆን ግን መልእክቱን በማውገዝ ድርጊቱንና ክፋቱን ቀጠለ ሌላውና ሦስተኛው ዲያቆን ግርማ በቀለ ደግሞ ነገሩን ሁሉ በጥንቃቄ ከተረዳ በኋላ ከማኅበሩ በመለየት ጉዳዩን በቅርብ ርቀት በመከታተል ራሱን አገለለ።

ከዚህ በኋላ መንፈሰ ዛር ያደረባት ሴትና ዲያቆኑ 10ሩን ሴቶች ስብስባ በመጥራት እገሌና እገሌ የተባሉትን ሰዎች እኔ ስላልመረጥኳቸው አባርሬያቸዋለሁ በማለት የዛሩ መንፈስ መግለጫ ሰጠ። ሴቶቹም በነገሩ ተደናግጠው እነሱንም እመቤታችን ተቆጥታ እንዳታባርራቸው በመማጸን ንሥሐ እየገቡ ይቅርታ ጠየቁ። ለጽድቅና ለኃጢአት ሥርየት ይሆናል እየተባለ በእመቤታችን ስም የሚሰበሰበው ብርም ከጊዜ ወደ ጊዜ እጅግ ከፍ አለ።

ደግሞም በእመቤታችን ተአምር ተብሎ ከቤት ውስጥ ከተሰበረ የውኃ ቧንቧ ብረት ላይ ውኃ ቢፈስ ጸበል ነው ተብሎ ሁሉም አባላቱ ሲጠጡት ኑረዋል። እንዲህ እንዲህ እያለ የቆየው ይህ የሰይጣን አሠራር ከዚህ ለየት ያለና እንግዳ ነገር ፈጠረ። የዛሩ መንፈስ ወረደና እኔ ማርያም ነኝ የማዛችሁን ሁሉ ማድረግ አለባችሁ አትጠራጠሩ ጥርጣሬ የመናፍቃን ባሕርይ ነው እናም የማዛችሁን ሁሉ በእምነት አድርጉት በማለት ከወዲሁ ለነገሩ ክብደትን ይሰጣል።

በማስከተልም "ድንግልናችሁ በተአምር የጋብቻችሁ ዕለት ይመለስላችኋል አሁን ግን ለዲያቆኑ ድንግልናችሁን ስጡት" ይባላሉ። እነሱም ይህን ያዘዘችው እመቤታችን ሆነችና ለታዘዘለት ዲያቆን ድንግልናቸውን ለመስጠት ወረፋ ተመዘገቡ። ይህ ሁሉ ሲሆን ነገሩ ሁሉ ከእመቤታችን እንደሆነ እንጂ ከሰይጣን ይሆናል ብለው ቅንጣት ታህል አልተጠራጠሩም። ይልቁንም የሚታዘዙትን አለማድረግ ለነሱ ትልቅ ኃጢአት ነበር መስሎ የሚታያቸው።

ዲያቆን እሸቱ ድንግልናቸውን ለማስገሰስ የተመዘገቡትን ልጃገረዶች ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ የአራቱን ሴቶች ድንግልና ወሰደ ከዚህ በኋላ ግን ዲያቆኑ ኩራት ኩራት ተሰማውና የሌሎችን ሴቶች ድንግልና ለመውሰድ ቀጠሮ በማራዘም አዘገያቸው። በእርግጥ

ከእርሱ እንደማያመልጡና የታዘዙትም ለእርሱ እንደሆነ አስረግጦ ስለሚያውቅ ሊኮራ ይገባዋል።

ከዕለታት አንድ ቀን ዛሩ ወረደና ሁሉንም ሰብስቦ እናንተ ለእኔ እንደ 12ቱ ሐዋርያት ናችሁ ተሸከሙኝና ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያኔን አዙሩኝ ብሏችው እነርሱም በታሪዛ አድርገው ዛር ተሸክመው ቤተክርስቲያኑን አዙረውታል። ከዚህ በኋላ ግን ዛሩ ከዲያቆኑ ጋር በመመካከር አደገኛ ዘዴ ፈጠረ ይህ የተሰበሰበ ብር ብቻ 40,000 ብር ደርሷል ጌጣ ጌጡ ደግሞ ተደማምሮ ወደ 57,000 ብር ከፍ አድርጉታል። ይህ ብር በባለ ዛሯና በዲያቆኑ እጅ ነው ያለው። ከዚህም ጋር ባለ ዛሯና ታናሽ እህቷ ከእናት ከአባታቸው የተሰጣቸው መኖሪያ ቤት ነበር ይህን መኖሪያ ቤት እህትማማቾቹ የጋራ አድርገው ይኖሩበት ነበር። አሁን ግን አንድ ልዩ ዘዴ ተፈጠረና ታናሽ እህቷን ገድላ ዲያቆኑን አግብታ ቤቱን ብቻዋን ወርሳ ያን የተሰበሰበ ብርም አብረው ሁለቱ ሊጠቀሙበት ተማከሩ።

የቅዱሳን ማኅበር የተባለው ይህ የሰይጣን ማኅበር አሁን ወደ ነፍሰ ገዳይነት ሊገባ ራሱን እያዘጋጀ ነው። አሁንም በአንድ አሐድ ሴቶቹ ሁሉ ተሰብስበው እያሉ ከአመቤታችን አዲስ መልእክት መጣ መልእክቱ "ከእናንተ መካከል እገሊት እንደ ይስሐቅ ራሷን ለመሥዋዕት ታቀርባለች በሦስተኛውም ቀን ትነሣለች እርሷም የተባረከችና የተመረጠች የእግዚአብሔር በግ ናት" በማለት ዛሩ የልጅቷን ስም ጠቅሶ ተናገረ። ልጅቷ የባለዛሯ ታናሽ እህት ናት ለወራሽነት ተቀናቃኝ ትሆናለች ተብሎ እንድትሞት ከእኅቷ ተፈረደባት።

ልጅቷም የሰይጣንን ምክር አላወቀችምና እንደ እግዚአብሔር መልካም ትዕዛዝ በመቁጠር ራሷን ለሞት አዘጋጀች። አሟሟቷ

በጨርቅ ታፍና አንገቷን በነጠላ ታንቃ ከቤት ውስጥ እንድትንጠለጠል ተደርጉ ነው።

ራሷን እንደ ይስሐቅ የቆጠረችው በሦስተኛው ቀን እንድትኖግ ቃልና ተስፋ የተገባላት የሰይጣን መሥዋዕት በተወሰነላት ቀን ራሷን ለሞት አዘጋጅታ መጣች። ፀጥታ እንዲሰፍን ለጊዜው በጸዕር ምክንያት ብትጮህም እንኳ በጸሎት ማገዝ እንጂ ሌላ ምንም ማድረግ እንደማይቻል ለአባላቱ ጥብቅ መልእክት ከእመቤታችን ተብየዋ ተላለፈ። ሟቿም መልእክቱን ከእግዚአብሔር በቀጥታ እንደተላለፈላት አድርጋ ተቀብላቸዋለችና ፍርሃት አልታየባትም። ከዚህ በኋላ ልጅቷ በመቀነቷ አንገቷን ታሥራ ተንጠለጠለች፣ አረፋ ደፈቀች፣ እንባ በእንባ፣ ጣር በጣር ተሞላች፣ ጥቂት ደቂቃዎች በስቃይ አለፉ፣ ጭንቁ በዛባት፣ ቶሎ መሞት አቃታት።

ከዚህ በኋላ ግን ወደ ልቧ ተመለሰች መንፈስ ቅዱስ ሹክ አላት። እግዚአብሔር እንደዚህ እንደማይፈትን፣ በምህረት የተሞላ አምላክ መሆኑና በክርስቶስ ደም የተዋጀሁ እንዴት በዚህ ጣርና ስቃይ እንድሞት ይፈልጋል? የሚል ትክክለኛ መንገድ አገኘች። ከዚህ በኋላ መታገስ አልቻለችም። ግን በጣም ደክማለች፣ የተንጠለጠለችበትን ጨርቅ በእጇ ያዘችና ጉሮሮዋን ትንሽ አላረፈች። ከዚያም ያላትን ኃይል ሁሉ አሰባስባ የድረሱልኝ፣ የአድኑኝ ጥሪዋን አስተጋባች።

ይህን ሁሉ ጉድ ሰምቶ የማያውቅ ጉረቤት የተፈጠረውን ነገር በውል ሳይገነዘብ ጩኸቱን ሰምቶ ብቻ እየዘለለ ገባ። እንድትሞት የፈረዱባት አባላት ሁሉም ስለ እርሷ ጸልዩ ተብለው በሌላው ክፍል ይጸልዩ ነበር። ከጉረቤት ያለው ሕዝብ ግን ዘው ብሎ ሲገባ ወጣቷ ብቻዋን በሞት ጣር እየተሰቃየች ነበር። በርብርቦሽ ከተሰቀለችበት ካወረዷት በኋላ ፖሊስ ጣቢያ በመደወል ሁኔታውን አሳወቁ። ፖሊስም

ፈጥኖ በመምጣት ወጣቷን ወደሕክምና ከወሰደ በኋላ ለምን እንደዚህ ያለ ነገር እንደፈጸመች ጠየቀ፣ እርሷም የተጠየቀችውን ሁሉ በዝርዝር ካስረዳች በኋላ እስከ አሁን የፈጸመችው ነገር ሁሉ ስሕተት እንደነበርና ለእግዚአብሔርም እንዳልሆነ በመገንዘብ እገሌ እገሊት እያለች ስም በመጥራት ማጋለጡን ተያያዘችው (የፖሊሱ መረጃ እንደሚያስረዳው)።

ይህን ወንጀል የፈጸመው ዲያቆን እሸቱም በቁጥጥር ሥር ዋለ። በወቅቱ እሑድ እሑድ ከ4:00 ሰዓት ጀምሮ የፖሊስ ፕሮግራምን ያቀርብ የነበረው ሻምበል ግዛው ዳኜ ነበር። ሻምበል ግዛው ለሞት የተዳረገችውን ሴትና ድንግልናቸው የተወሰደባቸውን ሴቶች ወደ እስቱዲዮው በመጋበዝ ሙሉ ታሪኩን እንድንከታተል አድርጉ ጋብዞን ነበር። ሴቶቹ ማለትም ድንግልናቸው በጋብቻ ጊዜ ይመለስልናል ብለው የተደፈሩት ሴቶች በግንባር በመቅረብ ሙሉ መረጃ ሰጥተዋል። 57,000 ብር የተገመተው ብርም ከእነርሱ እንደተሰበሰበ በግልጥ ተናግረዋል። ሁሉንም ያደርጉት የነበረው በእመቤታችን ትዕዛዝ እንደነበር ያምኑ ነበር።

ጋዜጣኛው ሻምበል ግዛው ዳኝ ለተወሰደባችሁ ድንግልና የምትሉት ካለ? ብሎ ቢጠይቃቸውም ይህን ጉዳይ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት ያውቃል ብለዋል። ዲያቆን እሸቱ ግን 8 ወር ከታሠረ በኋላ የዋስ መብቱ ተጠብቆለት ከእሥር ቤት ወጣ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ግን ዲያቆን እሸቱ የሐመር መጽሔት ዋና አዘጋጅ ሆኖ ዲያቆን እሸቱ እያለ ስሙን መጻፍ ጀመረ። አሁን ደግሞ ቄስ ሆኖ በመስቀል ያሳልማል ።

የማኅበረ ቅዱሳን አመሠራረት ይህ ሆኖ ሳለ ደርግ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ወደ ጦር ግንባር ለማዝመት ትምህርት ከድል በኋላ

በሚል መፈክር ብላቴን ካስገባቸው በኋላ በዚያው ወቅት የግንቦት ልደታን አስመልክቶ ከብላቴን ማሰልጠኛ በተዘጋጀው መንፈሳዊ ፕሮግራም በቀጥታ የተላለፈውን እንደመነሻ በማድረግ ማኅበራችን የተመሠረተው ያኔ ነው ለማለትና ለማደናገር ተሞክሯል ።

ማኅበረ ቅዱሳን ያ የሞተና የበሰበሰ ታሪክ የኔ አይደለም ለማለት የተመሠረትሁት ብላቴን ላይ ነው ይበል እንጂ ከዚህ መጥፎ ታሪኩ ማምለጥ አይችልም።

## ልብ እንበል

እንደ እነርሱ አባባል ብንል እንኳ ፦

ማኅበሩ የተመሠረተው በደርግ ጊዜ ብላቴን ማሰልጠኛ ላይ ነው እንበል ። ይህ የረከሰው ታሪካቸው የቀረበው ደግሞ ማኅበሩ ከተመሠረተ በኋላ በኢሕ.አ.ዴ.ግ ጊዜ ነው ። እኛም ያኔ ይህን ፕሮግራም በሬዲዮ ስንከታተል የነበረው ከ1983 ዓ.ም. በኋላ ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ተቆጣጥሮ ሁሉም ነገር ተረጋግቶ እኛም መንፈሳዊ ኮሌጅ ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ከገባን በኋላ ነው ። ታዲያ ይህ ማኅበር ነፍሰ ገዳይ አይደለምን ? በዚህ ታሪክ ላይ የቀነስነው ካልሆነ በቀር የጨመርነው አንዳች ነገር የለም ።

# ሌላው የዚህ ማኅበር

# ክፉት መምሕራንን ማሳደዱ በምን ምክንያት?

ይህ ማኅበር በሰፈር ልጆች ተመሥርቶ ሲንቀሳቀስ ለዚህ የተበላሸ ታሪክ ሲበቃ ጤናማዎች የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ሲሸሹት ዕውቀት የጎደላቸው ልጆች ብቻ ተለይተው ቀሩ ከመንፈሳዊ አባት

መጠጋት መንፈሳዊ ያስመስላልና ወደ ዝዋይ ተጠጉ። ምሥጢሩ ያልገባቸው እኒህ አባት አቡነ ጎርጎርዮስ ልጆቼ እያሉ አንቆለጳጳሷቸው ። / ለዚህ ውለታቸው ዛሬ ለአቡነ ጎርጎርዮስ ጽላት ተቀርጾላቸዋል ጸበልም በስማቸው ተሰይሞላቸዋል ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንም ሊታነጽላቸው ነው በስማቸው በተሰየመው ጸበል የጳጳሱ ፎቶ ከፊት ለፊት ተቀምጦ ሕዝብ እየተሳለመው የቅዱስ ጎርጎርዮስ ጸበል እየተባለ ሰይጣን ይጫወትብናል / ።

ከዚያም አዲስ አበባ ሲደርሱ እነ አባ ወልደ ትንሣኤን አስተምሩን በማለት መጋበዝ ጀመሩ ። ስማችንም ማኅበረ ቅዱሳን ነው ብለው ሲናገሩ አባቶችም በደስታ ተቀብለው ይመለሳሉ ይህ እኩይ ማኅበር ይህን ቅዱስ ስም መያዙ የግድ ያስፈልገው ነበር ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለነዚህ ሰዎች ሲናገር፦

"እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኰለኞች ሠራተኞች ናቸውና። ይህም ድንቅ አይደለም ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና እንግዲህ አገልጋዮቹ (ማኅበረ ቅዱሳን) ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም። ፍጻሜያቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል።" (2ኛ ቆሮ. 11 ፥ 13-15)።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በወቅቱ ዝናና እውቅና የነበራቸው ታላቁ ሰባኬ ወንጌል አባ ወልደ ትንሣኤ አፈ ጮሌው አባ ማርቆስ ተፈራ፣ አባ ብእሴ ሰላም ጓሌ ሆነው ማኅበሩን አሳደጉት፤ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት እየመጡ በትምህርት ቤቱ አዳራሽ ስብከቱ ቀጠለ። ከዚያም እያደገ ወደ ቤተ-ክህነት አዳራሽ ደረሰ።

ይህን በቅድስና የተዳደፈ ማኅበር ከጥንቱ ስለምናውቀው የእባልነት ጥሪ ሲያደርጉልን እንደማንፈልጋቸውና ይልቁንም ንስሐ መግባት እንዳለባቸው ነገርናቸው። በነገሩ ያፈሩት አባላት የጳውሎስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተሐድሶዎች ናቸው በማለት ስም ማጥፋት ተጀመረ። በዚህ አጋጣሚ ከጥንት ጀምሮ የነበረው ነገር ግን በደርግ ጊዜ የተዘጋው ሃይማኖተ አበው በጠቅላይ ቤተ ክህነት አዳራሽ ሰፊ ማዕደ እግዚአብሔር የወንጌል ትምህርት ማካሄድ ጀመረ። አንቱ የተባሉ አባቶችና ጥንቱንም የሚያውቁት ሊቃነ ጳጳሳት ወደዚህ ግዙፍና ታላቅ ማኅበር ዘወር አሉ። ታላቅ ድጋፍና እንቅስቃሴም ሰጡት። አሉ የተባሉት ሰባክያነ ወንጌልም የዚህን ማኅበር እንቅስቃሴ በብርቱ ደገፉት በዚህ ጊዜ ነበር የማኅረ ቅዱሳን የወገብ ጅማት የተፈታው።

ማኅበረ ቅዱሳን የቻለውን ያህል ስም ማጥፋቱን ቀጠለ። በአንድ በኩል በመናፍቃን መሣሪያ ይዘምራሉ ይላል፣ ይህ ግን ፈጽሞ ስሕተት ነበር። መሣሪያው ፕሮቴስታንት የሚባለው ድርጅት ስንኳንስ በኢትዮጵያ በጀርመን ሳይፈጠር በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ነበር። እነ አባ ጊዮርጊስም በድርሰታቸው "በነቀልቃለ ስብሐት ሐኪዮ ለአርጋኖነ ጎሊናየ" ማለትም በሚያነዋውጥ ምሥጋና የልቤን አርጋን ምችው፣ በማለት መሣሪያው ቀድሞም በሀገራችን እንደነበር አመልክተዋል።

ይህ ማኅበረ ቅዱሳን አንዱም እንኳ በቆሎ ትምህርት ቤት ያላደረ የቤተክርስቲያኒቱ ጠረን ያልነካው ጥንተ ታሪኳን የማያውቅ አሻቅቦ የሚፈስ ውኃ በዘረኝነት ገመድ ታሥሮ የሥልጣን ጥሙን ለማርካት የቆመ ነው። በሌላ በኩል ይህ ማኅበር ሃይማኖተ አበው የነፍጠኛ ሃይማኖት (የአማራ ሃይማኖት) ነው በማለት ስሙን አጥፍቶታል። እንደገናም የወቅቱን እንቅስቃሴ በማዳመጥ ሃይማኖተ አበው የመአሕድ ሃይማኖት ነው ማለት ጀመረ በዚህ ሁሉ አቅምና

ጉልበት ያጣው ማኅበረ ቅዱሳን ሰይፍና ጉመድ መዘዘ፣ ከዚያም በሐረር፣ በድሬዳዋ፣ በመቀሌ፣ በባሕር ዳር በማርቆስ ሰዎችን መግደል ጀመረ።

ይሁን እንጂ ማኅበረ ቅዱሳን በአሁኑ ሰዓት በአደገኛ ሁኔታ ወደ መንግሥት ባለሥልጣንነት እያደገና እየተደራጀም ስለመጣ ወደፊት ለአቡነ ጳውሎስና ለመንግሥት የጉን ውጋት እንደሚሆን ትንበያችን የማይጠረጠር ነው። እኛም ይህን በሽታውን ስለምናውቅበት መናፍቃን የሚል ስም እንደታርጋ ቁጥር ተለጥፎብን ከቤተ-ክርስቲያን ታዛ ተጠልለን እንኖራለን። እንዲሁ ግን ዝም አንልም የቤተ-ክርስቲያናችን በሽታ የሆነውን ይህን ማኅበር ለመገልበጥ በወንጌል ቃል ሰይፍ እንነሣለን። ሕዝባችንም እንዲህ ነው እንዴ በማለት ወደ እውነት ይመጣ ዘንድ ጥሪያችንን በማናቸውም መንገድ ለማስተላለፍ ቆርጠናል።

## የዘመናት ውሸት በቤተ ክርስቲያን

አሁንም እንዋሻለን መዋሸታችንን ልባችን እያወቀው ወደ እውነት ለመመለስ ሐፍረት እየተሰማን እስከ አሁን እንዋሻለን። በብዙ ውሸት ሀገራችን እውቅና አግኝታለች ታቦተ ጽዮን በኢትዮጵያ፣ ግማደ መስቀሉ በኢትዮጵያ፣ ድንግል ማርያም ተሰዳ የኖረችው በኢትዮጵያ ጻድቃን የተባሉ ሁሉ የተፈጠሩት በኢትዮጵያ መላእክት የሚዘምሩት በግዕዝ ቋንቋ፣ አዳም ንጣበር ተብሎ የተፈጠረበት በግዕዝ ቋንቋ፣ ለማርያምም፣ ለጊዮርጊስም ለአቡየም ለተክልዬም አሥራት የተሰጠች ኢትዮጵያ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው።

እንደዚሁ ስለቅዱስ ያሬድ ብዙ ተብሏል። በአሁኑ ሰዓት ያሬድ ከመላእክት አንዱ እንጂ ሰው መሆኑ እየተረሣ መጥቷል። እንደመነሻ የሆነን ይኸው የቅዱስ ያሬድ ታሪክ ነው። ያሬድ ብትግራይ ክፍለ ሀገር

ተወልዶ እድሜው ለትምህርት ሲደርስ ትምህርት ቤት እንደገባና ትምህርቱም እምቢ እንዳለው ብዙ ጊዜ ይተረካል።

ለሰባት ዓመታትም ያሕል ምንም ትምህርት ሳይገባው ቆይቷል ይባላል። ነገሩን መንፈሳዊ ለማድረግ ስለታሰበ ብቻ ሆነ ተብሎ ስለያሬድ ድንቁርና በሰፊው ተንጸባርቋል። ስለ ያሬድ ድክመትና ችግር ይህን ከገለጹ እግዚአብሔር እንዲህና እንዲያ አደረገለት እንዲህም ተገለጠለት ለማለት ያመቻል።

## ውሸት አንድ

ያሬድ ትምህርት እምቢ ብሎት ተስፋ ቆርጦ ወደ ቤቱ ሲመለስ ደክሞት ከዛፍ ሥር ተቀመጠ። በትምህርቱ ምክንያት እየተጨነቀ ነገር በልቡ ቋጥሮ ሲያወጣ ሲያወርድ አንድ ትል ወደ ዛፉ ሜፍ ለመውጣት ሲሞክር ሲወድቅ ብዙ ጊዜ ተመለከተው ያሬድ እኔም እንጂ እኔምኮ እኔም ተስፋ ሳልቆርጥ እንዲህ ደጋግሜ ብሞክር ይሳካልኝ ይሆናል በማለት እንደገና ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ መማር ጀመረ። ምሥጢረ ሰማይ ወምድር ተገለጠለት። ድርሰት መድረስ ቻለ ተብሏል።

## ውሸት ሁለት

አንድም አሉና ባለአንድምታዎች ያሬድ ትምህርቱ እምቢ ብሎት ከዛፍ ሥር ተቀምጦ ሲያለቅስ መልካቸው ቀይ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ የሆኑ ሦስት ወፎች መጥተው እዝል ግዕዝ አራራይ ዜማ ነግረውት እንደ ደረሰው እነዚያም ወፎች ሥላሴ እንደሆኑ ዜማውም እዝሉ በአብ፣ ግዕዙ በወልድ፣ አራራዩ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚመሰል አድርገው አስተምረዋል።

# ውሸት ሦስት

ቀጠሉና ባለአንድምታዎች ይህስ አይደለም ብለው ከላይ ሲገልጡት የነበረውን ሁሉ አፍርሰው ቅዱስ ያሬድ ትምህርት እምቢ ብሎት ወደቤቱ ሲሄድ ከዛፍ ሥር ተቀምጦ ሳለ ከትሉ እንደተረዳው እኔም ተመልሼ ብሄድ እንደዚህ እሆናለሁ ብሎ ሲመለስ መላእክት ወደሰማይ ነጥቀው ወስደው ከ24ቱ ካህናተ ሰማይ ጋር ቀላቀሉት። ከእነርሱ ጋርም በእነሱ ዜማ አብሮ አመሰጋገኑ ተገልጦለትም ወደ ምድር ይዘት መጣ ብለዋል።

እንዲህ ከሆነ በወቅቱ የነበረው ብሔራዊ ቋንቋ ግዕዝ ነበር። ያሬድም የሚያውቀው ይህንኑ ቋንቋ ነው። በሰማይም ሄዶ ያመሰገነበትና ከመላእክት ጋር ድምጹን ያስማማበት ይኸው ግዕዝ ሊሆን አይደለምን? መልካም የያሬድ የዜማ መሣሪያ የተባሉት ሁሉ ከበሮ፣ ጸናጽል መቋሚያ ሁሉ በሰማይ አሉ ማለት ነው። እውነት ቢሆንና ዜማችን ከመላእክት የመጣ ከሆነ እጅግ የተባረከች የተቀደሰች አገር ናት። ከመላእክት ከተማም አንዷ ናት።

የሕይወት ታሪኩን በዚህ እናቁምና ሐመር መጽሔት 7ኛ ዓመት ቁ. 3 ሰኔ/ሐምሌ ብሎ ባወጣው ዘገባ የያሬድን ድርሰት እንመልከት። ያሬድ በድጓው መገሠጼ ዳዊት ጠቅሶ "መሠረታቲሃ ውስተ አደባር ቅዱሳን..." ብሏል። ትርጉሙም "መሠረቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ....." ማለት ነው (መገ. 86(87):1) በቅዱስ መጽሐፍ ደግሞ "መሠረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው" ይላል። ግዕዙ "መሠረታቲሃ" ብሎ ለሴት ቢያደርገውም አማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ "መሠረቶቹ" ብሎ ለወንድ ቀጽሎታል።

ይህን ክፍል ሐመር የተባለው መጽሔት እንዴት እንደተረጐመው እንመልከት "የቤተ መቅደስ መሠረቶቿ ለእግዚአብሔር የቅድስናው ቦታ በተለዩ ተራሮች ውስጥ የጸኑ ናቸው" ብሏል (ገጽ. 10) የተዘበራረቀ ትርጉም ያለው ይህ መጽሔት በዚህ መነባንብ ቤተ መቅደስን ባለቤት ካደረገ በኋላ የያዘውን ዘንግቶ ለማርያም አድርጉታል እልፍ አለና ገቢር ተገብሮ አድርጉ በከርሣ ተጸውረ በማለት ባለቤቱን ለእግዚአብሔር አድርጉታል። መቼም ዛሬ ዛሬ ነገሮቻችን ሁሉ ባለቤተ ብዙ እየሆኑ ስለመጡና ስለተለመዱ ቤተክርስቲያን ታዛ ሆነን የምንዋሸውም ውሸት ተቀባይነትን ስላገኘልን ፍርሐተ እግዘአብሔርን ከልባችን አስወግደን በድፍረት ተሞልተን ያሻንን ሁሉ እንናገራለን።

በተለይም አቡነ እገሌ ቅዱስ እገሌ ብለን የምንመሠርታቸው ትምህርቶች ልዩ የሆነውን የልባችንን ምኞት እንድንናገር ስለሚያመቹን መተግኛ ዋሻ ሆነውናል። የሕዝባችንን አለማወቅ ያስተዋሉት ጮሌዎች በሕዝቡ ሥነ ልቡና በመረማመድ አደገኛ መልእክት እያስተላለፉ ነው። በአሁኑ ሰዓት የያሬድ ድርሰት የትኛው እንደሆነ እስከማይታወቅ ድረስ በየጊዜው የተነሡ ደባትሮች ስለጨመሩበትና ስለከለሱት ይህም "ዘአንበሩ አበዊነ" ተብሎ ተቀባይነትን ስላገኘ ከሰማይ የወረደ ያሕል ቆጥረን ተቀብለነዋል። ለምሳሌም መጽሐፈ ዚቅ በአጼ ኢያሱ እድያም ሰገድና በዓፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ተደረሰ ይላል። ራሱ መጽሐፈ ዚቅ መቅድም የተክሌ አቋቋም ዝማሜም በአለቃ ገብረ ሐና ልጅ በመምህር ተክሌ የዛሬ 130 ዓመት አካባቢ ተደረሰ ይባላል።

እንዲህ እየተደረገ የተጨመረው ሁሉ የያሬድ ይባላልን? ከያሬድ በኋላ ለተነሡ ቅዱሳን ሁሉ ዋዜማና ክብረ በዓል ተዘጋጅቶላቸው

ሲወደሱ ሲሰለሱ ይውላሉ ለነዚህ ሁሉ ያሬድ እንዳልደረሰላቸው ሊቃውንቱ ሁሉ ይመሰክሩታል ግን ሁሉም ድርሰት በያሬድ ስም እየተጠራ ስሕተት ያለበት ጓዝ ሁሉ የቅዱስ ያሬድ ነው እየተባለ እንዳይስተካከል እንኳ የመንፈስ ቅዱስ ድርሰት ነው እየተባለ ተፈርቶና ተከብሮ ይኖራል። የዚህም ከፍተኛ ሚና ተጫዋች ሐመር መጽሔት ነው። መናፍቅ ተሐድሶ የሚለው ስም ከነሱ በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር ስለራቀ የሚናገሩት የሚጽፉት ሁሉ ተአማኒነት አለው። ግን ልንባንንበት ይገባል።

ሐመር በዚሁ ዘገባውና ጥናቱ አያይዞ ያቀረበው ደግሞ አዳም በልጅ ልጅ እንደሚድን የተሰጠው የ5,500 ዘመን ተስፋ ድኅነት ይላል። ይህም ከያሬድ አባባል የተጠቀሰ ሲሆን ቃሉ የሚለው "ምስሌከ ቀዳማዊ በዕለተ ኃይል፣ በብርሃኖሙ ለቅዱሳን፣ ወለደ ኩከ እምከርሥ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ ጸረቆ በከርሣ ውእቱኒ ቀደሳ ወይቤሎ ለእቡነ አዳም እትወለድ እምወለትከ ወእድሕክ ውስተ መርዓነከ ወእከውን ሕፃነ በእንቲአከ" (መዝ. 109፡31) ይላል ትርጉሙም "ከአንተ ጋር ቀድሞ በኃይልህ ቀን በቅዱሳን ብርሃን ከእግቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ እርሷ እርሱን በሆዷ ተሸከመችው እርሱም እርሷን ቀደሳት አባታችን አዳምን እንዲህ አለው ከልጅህ እወለዳለሁ በሜዳህም እድንለሁ ስለአንተም ሕጻን እሆናለሁ" ይላል (ሐመር 7ኛ ዓመት ቁጥር 3 1991 ሰኔ/ሐምሌ)

መጽሔቱ ማጣሪያ ወንፊት ስለሌለው አሠሩንና ግስንግሱን ሁሉ እየለቃቀመ ይመግባል። ስለዚህም ጤናማ አካል የለውም የያሬድ ተብሎ የቀረበው ይህ ድርሰት ግማሽ ከመዝሙረ ዳዊት 109፡3 የተወሰደ ሙሉ ቃል ሲሆን የቀረው ደግሞ እግዚአብሔር ለአዳም ተናገረው የተባለው ቃል ነው ምንጩ/መነሻው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሆኖ

ሌላውና ቀጣዩ ግን ልዩ ፈጠራ እግዚአብሔርም ያልተናገረው እንግዳ ቃል ነው። እግዚአብሔር ተናገረው የተባለው ቃል በዘፍጥረት 3÷15 ያለው ብቻ ነው። እንደ አባዜ ሆኖብን ከእውነት ላይ ካልጨማመርን እሺ አይለንም እንጂ እውነቱ ከሐመር መጽሔት የራቀ ነው። ያላሉትን አሉ እያልን የአርጊት ተረት ይመስል በእግዚአብሔር ቃል ላይ እየጨማመርን ከቆየን ውለን አድረናል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሁለተኛ ጊዜ በጻፈላቸው በቆሮንቶስ መልእክቱ "ነገር ግን የሚያሳፍረውን ስውር ነገር ጥለናልና በተንኮል አንመላለስም የእግዚአብሔርንም ቃል በውሸት አንቀላቀልም እውነትን በመግለጥ ግን በእግዚአብሔር ፊት ለሰው ኅሊና ሁሉ ራሳችንን እናመሰግናለን" (2ቆሮ4÷2) ብሏል።

እንዲህ ያለውን ጤናማ ቃል ሰምተን ከራሳችን ወንጌል ወጥተን ለመዳን አልታደልንም። ጤናማው ወንጌልም ከእኛችን እየወጣ ነው። በመሠረቱ ደግሞ የዜማ ሰው መሆንና የመጻሕፍትን ምሥጢር መመርመር ድርሰትንም መድረስ ሁለቱ የተለያዩ ናቸው። ያሬድ የዜማ ሰው ከሆነ፣ ከዚህ ማለፍ የለበትም ድርሰት ለመድረስ ግን ብሉያትንና ሐዲሳትን ጠንቅቆ ማወቅና መረዳት ያስፈልጋል። አሊያማ መንፈስ ቅዱስ አደሮብኛል፤በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቻለሁ ብለን እንደስሜታችን የምንደርስ ከሆነ ነገሮቻችን ሁሉ ከቅጽረ ወንጌል ወጥተው በከሀደት ሜዳ የሚሩጉ ይሆኑብናል። ለዚህ ለዚህማ እነባሕታዊ ገብረ መስቀል መቼ አነሱን? እንግዲህ ግን በቅዳሳን ስም ሰይመን ከላይ የሰቀልናቸው መጻሕፍት ሁሉ እየተመረመሩ ለእውነተኛው ወንጌል ቦታቸውን ቢለቁ ይበጃል እስከመቼስ እየዋሸን እንኖራለን?

ቅዱስ ያሬድ ከሰማይም ያምጣው ከምድርም ያውጣው የዜማ ሰው እንደ ነበርና በነገሥታት ፊት (ለነአጼ ገብረ መስቀል) መወድስና

ወረብ እያቀረበ እንደነበርና ከአባ አረጋዊ ጋርም የቅርብ ግንኙነት እንደነበረው በታሪክ ይነገራል። ያሬድ ትምህርት ተገለጠለት እንጂ አዲስ ድርሰት አላመጣም። ድጓውም ጸዋትወ ዜማው ሁሉ ከመጀመሪያ ጀምሮ ነበር የሚሉ ሊቃውንትም አሉ። ደግሞም ይመስላል ለመሆኑ ያሬድ አልገባው ያለው ድጓው ነው? ወይስ ቅዳሴው? በዚያን ዘመን የነበረው መንፈሳዊ ትምህርትስ ምን ነበር?

እንዱ ሐመሮችን የጌታችን የትውልድ ሐረግ ትክክል ሊመጣልኝ አልቻለም በማለት ከኢኮንያን እስከ ክርስቶስ ያለው 14 ትውልድ ይላል ቆጥሬው ሊመጣልኝ አልቻለም? ይላል ጠያቂው። መልሱ በትክክል ይመጣል ጠንቅቀህ ቁጠረው መባል ነበረበት በትክክል ከተቆጠረ ከኢኮንያን እስከ ክርስቶስ 14 ትውልድ ነውና። ሐመሮች ያልተጠየቁትን እንመልሳለን ብለው የተሳሳተ ትምህርት አስቀምጠዋል።

ስሕተቱ የተፈጠረው ዮሴፍንና ማርያምን ባሥጋ ለማዛመድ በተፈጠረ ጥበብ ነው። ማርያምና ዮሴፍ ዘመዶች ከሆኑ ደግሞ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አይተዋወቁም ለማለት እንዲያመች ነው። ይህ አባባልና ጥበብ ግን ከመላ ምትነት አያልፍም። ከዚህ ይልቅ የተሻለውና እውነተኛው ነገር እንደ ቅዱስ መጽሐፍ አባባል መቀበል ነው። ድንግል ማርያም ስለእናትና አባቷ ምንም የተገለጠ ነገር ሳይኖር በገሊላ አንዲት ድንግል ነበረች የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ። ተብሏል።

ምንም እንኳ ድንግሊቱ ያለእናትና ያለአባት እንዳልተወለደች ብናምንም ስለዘር ሐረጓ ስላልተገለጠልን ዝም ማለቱ ይመረጣል። አይሁድ ማርያምን ለዮሴፍ በእሪጫነት መስጠታቸው ዝምድናውን እያወቁ አይደለም። ዝምድና እንደሌላቸው ዘራቸውን ተንትነው የሚቆጥሩት ፈሪሳውያን በሚገባ ያውቃሉ። እግዚአብሔርም

"ማንም ሰው ከሥጋ ዘመዱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አያድርግ" ሲል አዝዟል (ዘሌ. 18፡6-18) ይህንም ትዕዛዝ ለመሻር ዘመድ ከዘመድ ለማጋባት አያስተጫጩም።

ደግሞም ስለማርያም ማንነት የሚያውቅ ወይም የተረዳ አንድም ሰው አልነበረም። እርሷም ራሷ መልአኩ እስኪነግራት ድረስ ስለራሷ የምታውቀው ምንም ነገር አልነበረም። ጌታን እንደምትወልድም አታውቅም ነበር። መልአኩ ገብርኤል "ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ" ሲላት "ይህ እንደምን ያለ ሰላምታ ነው" ብላለች ድንግል ማርያም ወደፊት ትዳር የመያዝና ልጅ የመውለድ እቅድ ቢኖራት እንኳ መልአኩ ትወልጃለሽ ሲላት ከዮሴፍ ስለምወልድ ይህ ተነገረኝ ብላ ትቀበለው ነበር እንጂ "ወንድ ሳላውቅ ይህ እንዴት ይሆንልኛል" ለማለት ባላስፈለጋት ነበር። እንደሰውኛው ዘይቤ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታለች እንደ እግዚአብሔር እቅድ ደግሞ ከዚህ በስተጀርባ ነው። ከመውለዷ በፊት የነበራት ሕይወት "የድንግሊቱ" ሲል ድንግል እንደነበረች እንረዳለን ።

እንግዲህ ድንግል ማርያምና ዮሴፍ ዘመድም ይሁኑ ባዕድ እርሱኛሞች እንደነበሩና ነገር ግን ምንም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስረዳል። ዮሴፍ በማያውቀው ምሥጢር እርሱኛው ጸንሳ ቢያገኛት በሥውር ሊተዋት አሰበ እንጂ ሊያስወግራት አልፈለገም።

በትክክልም እርሱኛዋ ስለነበር የዘር ቆጠራው በእርሱ በዮሴፍ በኩል ተደርጉ ተቆጠረ። ዮሴፍም እንደ ሥጋ አባት በመሆን የኢየሱስ ክርስቶስን የትውልድ ሐረግ በእርሱ በኩል አስመዘገበ ትውልዱም አልዓዛር ማታንን ወለደ፣ ማታንም ያዕቆብን ወለደ፣ ያዕቆብም ዮሴፍን ወለደ እርሱም የማርያም እርሱኛ ነበር (ማቴ. 1፡15)። ዮሴፍ የዘር

ሐረጉ በአብርሃም በዳዊት በኢኮንያን፣ በዮሴፍ በኩል ነው። በዚህም የዳዊት ዘር ተብሏል። ስለድንግል ማርያም ግን የተገለጠ ነገር የለም። በመንፈስ ቅዱስ የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ እንድናውቀው የተፈቀደልንን ነገር መዝግቧል። በእርሱ ያልተገኘውን ታሪክ በመለቃቀም እንዲህ እንዲያ እያልን የምናወራ ከሆነ ከእውነት ሐሳብ ስለምንወጣ መጽሐፍ ቅዱስ ካቆመበት ቦታ ላይ መቆሙ ብልህነት ነው።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ድንግል ማርያም ዘመትር ድንግል ናት መቼም ቢሆን እስከ መጨረሻው አግብታ ወለደች የሚል ታሪክ የለንም፣ ከእፎኝነት በመነደርደር ወደ ጋብቻ የምናስጠጋት ከሆነም የተሳሳተ ግንዛቤ ይሆንብናል። ሐመሮች ደግሞ በዘኩላቸው በማቴዎስና በሉቃስ የአጻጻፍ ስልት ገብቱው ማቴዎስ እንደዚህ ሉቃስም እንደዚያ ጽፏል በማለት በሁለቱ ወንጌላውያን መካከል ያለውን ክፍተት ለመሸፈን ሞክረዋል። በመሠረቱ ሁሉም ወንጌላውያን በትክክል ጽፈዋል። አናበላልጥም ሁሉንም ያጻፈ መንፈስ ቅዱስ ነውና ሐመሮች የሌለ የዘር ቆጠራ ውስጥ ገብተው። የፈጠራ ታሪክና የራሳቸውን መላምት ሰግስገውበታል። ከዚህ ወጥተው እንደ ወንጌላውያን እንደ ማቴዎስ ማርቆስ ሉቃስና ዮሐንስ ቢያስተምሩ ይመረጣል እንላለን።

## <u>ማጎበረ ቅዱሳን</u>

"የሞቱ ዝንቦች የተቀመመውን የዘይት ሽቱ ያገሙታል እንዲሁም ትንሽ ስንፍና ጥበብንና ክብርን ያጠፋል የጠቢብ ልብ በስተቀኙ ነው። የሰነፍ ልብ ግን በስተግራው ነው። ደግሞም ሰነፍ በመንገድ ሲመላለስ እርሱ ልብ ይጐድለዋል። የሚያስበውም ሁሉ ስንፍና ነው" መጽሐፈ መክብብ 10፥1-3

በዓለማችን ዝናንና ክብርን ካገኙት ክላይንቲስቶች መጻሕፍት ይልቅ ለንግሩ ሁለትዮሽ ወይም ጥርጣሬ የሌለበት እኛ ባናምነውም እንኳ እውነትን የተሞላው ቅዱስ መጽሐፍ ታላቅ ነው። ቅዱስ መጽሐፍ ሁለገብ (ሥጋዊ ወመንፈሳዊ) የሆነ ለሰማያዊውም ለምድራዊውም ዓለም አስፈላጊና የዘወትር፣ የዘለዓለምና ወቅታዊ የሆነ፣ ጊዜው አይደለም ተብሎ የማይጣልና የማይናቅ የጠቢባንን ልብ እንዳንጠለጠለ የሚኖር ለዘወትር ብርቅዬ መጽሐፍ ነው። ሳይንቲስቶች ከመገኘታቸው በፊት ይኸው መጽሐፍ ስለጥበብና ስለጥበበኞች ተናግሯል። መጽሐፉን ከልብ ላስተዋለውና ለተመለከተው የኔ መጽሐፍ ነው የማይለው ሰው አይኖርም። ሰዎች የሚመረምሩት ሳይሆን የሰዎችን ልብና ኩላሊት የሚመረምርና አጥንትን፣ ቅልጥምንና ጅማትን የሚወጋ ቃል ያለው ልባዊ መጽሐፍ ነው።

የተጻፈው በመንፈስ ቅዱስ ስለሆነ አንባቢውም በመንፈስ ቅዱስ ሆኖ ካላነበበው ትርጉሙን ላያገኘውና ሊሳሳትበት ይችላል። ነገሩን ሲጀምር "ከንቱ ከንቱ የከንቱ ከንቱ" ብሎ የጀመረው ጥበበኛ "የሞቱ ዝንቦች የተቀመመውን የዘይቱን ሽቱ ያገሙታል" ብሏል።

**ዝንቦች**:- ዝንቦች በተፈጥሮአቸውና በባሕርያቸው ንጽሕና የሌለውን ነገር የሚወዱ፣ ቆሻሻ ቦታ ላይ የሚፈጠሩና የሚገኙ ለሰው ልጆችም ጠንቆች ናቸው። ጽዳታቸውን ባልጠበቁ በሽተኞች ሰዎችና ሕጻናት፣ በቆሰለ ሰውነት ላይም በመቀመጥ በሁለንተናቸው የተሸከሙትን በሽታ ወደጤናማ ሰው ያስተላልፋሉ። በተቀመመና በተነጠረ ነገር ላይ አርፈው ከዚህ ላይ ቢሞቱ ያ የተቀመመና የተነጠረ ነገር ጣዕሙንና መዓዛውን በማጣት ከጥቅም ውጭ ይሆናል። እኒህ ፍጥረታት ለሰው ምንም ጠቃሚ ነገር የሌለባቸው፣ አስቀያሚ ፍጥረቶች ናቸው። ዝንቦች ይህን ያሕል ለሕይወታችን ጠንቆች እንደሆኑ ሁሉ "እንዲሁ ትንሽ ስንፍና ጥበብንና ክብርን ያጠፋል"።

ስንፍና፦ ስንፍና ድካም አይደለም መለገምም አይደለም። መሥራት እየቻልን ጉልበቱ እያለን ሊሠራ የሚገባውን ነገር በተነሣሽነት አለማድረግ ወይም አለመሥራት ነው። ስንፍና ሐኬት የሚለውን ትርጉም ይሰጠናል። ስንፍና አላዋቆችንና ዋዘኞችን ከሐዲዎችንም ያካትታል። ሰነፍ አእምሮውን ሥራ ስለማያሠራው በልቡ እግዚአብሔር የለም ከማለት ይደርሳል። ይህም የስንፍና አንዱ ባሕርይ ነው። እንግዲህ ስንፍና ለማናቸውም ሥራ ተነሳሽነት ያለውን ሰው ሁሉ እንዳይሠራ ጉታችና አእምሮንም የሚያሥር ስለሆነ ጥበባችንንና እውቀታችንን ያጠፋብናል። ምግባረ ሃይማኖት የሌለን ያደርገናል ስለዚህም ሃይማኖታችንን ሥራ አልባ፣ ፍሬ አልባ፣ በማድረግ የሰውን ማንነት የሚያበላሽና የሚያቆሽሽ ነው።

በስንፍና የተያዘ ሰው በሃይማኖት ጤናማ የሆነ ኀይል ቢኖረው እንኳ በያዘው ስንፍና እንዲሳብና እንዲያገ በማድረግ የኀይሉንም ሕይወት እንዲበክል ያደርጋል። ስለዚህ ከሰነፎች ምክርና ትምህርት መራቅ ይጠበቅብናል። አንዳንድ ክርስቲያኖች ከሞዕመናን ጋር መውጣታቸውንና መግቢታቸውን እንደ ክርስትና በመቁጠር ተዘናግተው ይኖራሉ ማለትም ለውስጣዊ ማንነታቸው ትኩረት አይሰጡትም እነዚህ ግን ከሞቱ ዝንቦች የሚያንሱበት ባሕርይ አይታይባቸውም።

ስም ይዘን ነገር ግን ስማችን ከመቃብራችን በላይ ሆኖ ስለተጠራ ያለን እየመሰለን ራሳችንን በማታለል ዘመናችንን እንገፋለን፣ ራሳችን ያለበት ጠፍቶን በሰው ቦታ ሆነን የሰው ኑሮ እንኖራለን። ራሳችንን ፈልገን አጥተነዋል፣ ፈልገንም አላገኘነውም ይህም በመሆኑ ለንሥሐ አልታደልንም። ዛሬ ዛሬ በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ያለውን ሁኔታ በጥልቀት ስንመለከተው ጥቂት የማይባሉ ቅዱሳን ዋጋ የከፈሉበት ትክክለኛው አርቶዶክሳዊነት ከቦታው ተነቅሎ ፣ጠፍቶ በምትኩ ሌላ አርቶዶክስ ገብቶ፣የነበረውንና የክርስቶስ አርቶዶክስነት

ለማምጣት የሚደረገው የዛሬው ጥረት ከፍተኛ ዋጋ ይጠበቅበታል። ከፍተኛ ዋጋ ከሚከፈልባቸው ዋና ዋናዎቹ ሦስት ናቸው።

**አንደኛው፦** ሕዝባችን በልማድና በባሕል ሃይማኖት መያዙና ይህን የያዘውን ሃይማኖት ለመጣልና ለማጣራትም በቂ ዕውቀትና ግንዛቤ ስለሚጉድለው በራሱ አንብቦ መረዳት ስለማይችል።

**ሁለተኛው፦** ፎሌዎችና ክፉዎች ሳይማሩና ሳይገባቸው ያንኑ የያዙትን የተቀላቀለ ኦርቶዶክስነት ለማስተማር መደራጀታቸው ከዚህ የተነሣ የደንቆሮ ደጋፊው ብዙ ነው እንደሚባለው አብዛኛው ሕዝባችን እነሱን መከተሉ።

**ሦስተኛው፦** በአመራር ላይ ያሉት አባቶች ሥልጣናቸውንና ጥቅማቸውን የሚያስከብር ደንብ ብቻ አውጥተው የራሳቸውን ጥቅምም አስከብረው ሌላውን ችግር ግን በፊት የተበላሸውን አሁን ማስተካከል ይከብዳል በማለት ለግድየለሽነት ገዘም ማለታቸው ይህም አልበቃ ብሎ ለወንጌል አገልግሎት ብቁ ያልሆኑትን በመሾም መንጋዎችን በማስበላታቸው ነው። የሚሉትና ሌሎችም ችግሮች ናቸው።

የመሪዎች ገዘምታና እውቀት ማነስ በተበላሸ ሥነምግባርና በተሳሳተ ዶክትሪን ተመሥርቶ ቤተ ክርስቲያኒቱን እንዲቆጣጠራት ለማዝረ ቅዳሳን ትልቅ ክፍተት በመስጠት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። መሪዎች ሳይቸግራቸው ገፍተው ገፍተው ከላይ የሰቀሉት ይህ ማኅበር መንግሥት በማያገባው ጣልቃ እስኪገባ ድረስ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ፈታኝ ነገር ሆኖባታል።

ጥቂት የማይባሉ ጳጳሳትን በጥቅማጥቅም፣ በዘረኝነትና በከንቱ ውዳሴ በመዳፉ ሥር ያስቀመጠው ይህ ወጊ ማኅበር ከጅምሩ

በናዝሬትና በዙዋይ አካባቢ ሲንቀሳቀስ የበከተና ርኩሰትን የተሞላ አካሄድ እንደነበረው ፖሊስና እርምጃው በጋዜጣና በሬዲዮ ሲያስተላልፍን ቆይቶ ነበር። የፍርዱን አፈጻጸምና ውሳኔ እየተጠባበቅን እያለ ተድበስብሶ ቀረ። በእርግጥ ዓለማችን ወንጀለኛውን ያለፍትሕ ጻድቅ፣ ጻድቁንም በግፍ ኃጥዕ ማለቷ የታወቀ ነገር ነው። ሆኖም ማኅበሩ ግን ጉመናዬ ተደብቆ የቀረልኝ እዳይመስለውና አንገቱን እንዳያቀና በእጃችን የያዝናቸው አያሌ መረጃዎች ለሕዝብ መውጣት ጀምረዋል።

የሰዎችን ኃጢአት ለመግለጥ የተነሣሣነው እንደበጉ ነገር ቆጥረነው ሳይሆን ሕዝባችን ከክፉ መንገዱ ተመልሶ ራሱን በመመርመር ወደ ቅድስት ቤተክርስቲያኑ እንዲመለስ ብቻ ነው። እንደገናም ይህ ማኅበር ቤተ ክርስቲያኒቱን ሊወክል ስለማይችል ለቤተ ክርስቲያን ልጆች ቦታውን እንዲለቅ ብቻ ነው። ከዚህ ያለፈ ልዩ ተልዕኮ የለንም ተልዕኮአችን ሕዝባችንን ወደ ወንጌል መመለስና ከክርስቶስ ጋር ኅብረት እንዲያደርግ እርሱን ብቻ እንዲያመልክና ለእርሱ ብቻ እንዲኖር ማድረግ ነው። ዛሬ ለጥቅሙ ሲል ሕዝባችንን ሽባ በሆነው ትምህርቱ ከኔ ወዲያ አርቶዶክስነት ለኃጣር ብሏል በእርግጥ ማናቸውም የስሕተት ድርጅት ራሱን አርቶዶክስ ብሎ መሰየም ይችላል። አርቶዶክስ በመባሉ ግን አርቶዶክስ አይሆንም ትክክለኛ አርቶዶክስነት በክርስቶስ ሆኖ መገኘት ብቻ ነው።

## ዮሐንስ መጥምቅ

ነቢዩ ኢሳይያስ "በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምጽ" ብሎ የተነገረለት ይህ ዮሐንስ ከአባቱ ከዘካርያስ ከእናቱ ከኤልሣቤጥ ተወለደ። እናትና አባቱ በእድሜ ያረጁ ነበሩና ከእንግዲህ በኋላ ልጅ አንወልድም ብለው ተስፋ ቆርጠው ነበር። ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ

ገብርኤል የተባለ መልአክ እንኳ ልጅ ይወለድልሃል ማለትም ሚስትህ ኤልሣቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች ብሎ ሲያበሥረው እኔ ሽማግሌ ነኝ ሚስቴም በእድሜዋ አርጅታለች ነበር ያለው። እግዚአብሔር ሊሠራው ያለው ሥራ ነበረውና በዘካርያስ ዘር መድረቅ በኤልሣቤጥ ደም መቋረጥ ዕቅዱ አልተከለከለም። ዘካርያስ የዘር ፍሬ አፈራ ኤልሣቤጥም ማኅፀኗ ልምላሜን አገኘ።

ዘመድ አዝማድ አገር ጉረቤት ይሆናል ብሎ ያልጠበቀው ተአምር በነዚህ አረጋውያን ሕይወት ሲከናወን ሁለቱም በዕድሜያቸው ያረጁ ከመሆናቸው የተነሣ እንዴት ፍትወት ሊሆንላቸው ቻለ? የሚለውን ሐሜት ኤልሣቤጥ መቋቋም እንደሚሳናት ተረድታ ራሷን ስድስት ወር ያህል ከሰው ደበቀች፣ አልታይ አለች። የኤልሣቤጥን መጽነስ ካበሠራት መልአክ ከባሏና ከራሷ በስተቀር ማንም አላወቀባትም ነበር።

ኤልሣቤጥ በጸነሰች በስድስተኛው ወር ያው መልአክ ወደ እንዲት ድንግል ለተመሣሣይ ጉዳይ ተላከ በድንግልና እንደምትወልድ ለድንግሊቱ ሲያበሥራት ነገሩ ቢከብዳት ለእግዚአብሔር የሚሣነው ነገር የለም ኤልሣቤጥ ዘመድሽም በእርጅናዋ ጸንሳለች በማለት ምሥጢር አካፈላት። በነገሩ የተገረመችው ድንግል እንደ ቃልህ ይሁንልኝ ብላ ወደ ዘመዷ ኤልሣቤጥ በረረች። እንግዲህ ማርያም የዕለት ጽንስ ኤልሣቤጥ የስድስት ወር ጽንስ ይዘው ነው የተገናኙት በዚያኑ ዕለት ማርያምም በአጋ የተሞላች እናት ሆናለች፣ ኤልሣቤጥም የድንግሊቱን ድምጽ ስትሰማ መንፈስ ቅዱስ ሞላባትና የጌታዬ እናት ስትል ኃይለ ቃል ተናገረች።

ከሰላምታቸው በኋላ ተያይዘው ወደቤት ገብተዋል ማርያምም ለሦስት ወር ያህል በኤልሣቤጥ ቤት ቆይታለች በፊት ስድስት ወር

ነበራት አሁን ሦስት ሲጨመር ዘጠኝ ወር ይሆናል። ይህም የመውለጃዋ ጊዜ ነበር ማለት ነው። አስቀድሞ በአብሣሪው ስሙ ዮሐንስ እንዲባል ተወስኖ ነበርና ስሙ ዮሐንስ ተባለ። አደገ በመንፈስ ጠነከረ ሆኖም ለእሥራኤል እስከታየበት ቀን ድረስ በምድረ በዳ ኖረ ዮሐንስ ከተወለደ ከስንት ቀን ወይም ከስንት ዓመት በኋላ ከቤተሰቡ ተለይቶ በምድረበዳ ኖረ? በዚያስ ለስንት ጊዜ ያህል ቆየ? በማለት ከቅዱስ መጽሐፍ አልፈን ጥናት አናካሄድም ምክንያቱም አስፈላጊያችን ቢሆን ኖሮ ቅዱስ ሉቃስ አንድም ነጥብ ሳያስቀር ሁሉንም ብትንትን አድርጉ በጻፈልን ነበር። ስንኪንስ የባሪያው የዮሐንስ ታሪክ ይቅርና የንጉሡ የክርስቶስ እንኳ ለደኅንነታችን ብቻ የተመደበው ነው የተጻፈው ምክንያቱም የግል ሕይወት እንጂ ማኅበራዊ አገልግሎት አይደለምና ነው።

በምናልባት በምዕናብ እናውራ ከተባለ ምናልባት ሄሮድስ ሕጻናትን በገደለበት ጊዜ እናቱ በረኃ ወስዳው ነበር ማለት ነው። በዚያም የታዘዘ የእግዚአብሔር መልአክ እየመገበው ቆይቷል ማለት ነው። ከዚህ የተሻለ የምንመለምለው መላ አይኖረንም። ዮሐንስ የምድረ በዳ ኑሮውን ጨርሶ 30 (ሠላሳ) ዓመት ሲሞላው ወደ እሥራኤል ምድር መጣ። በዚህ ላይ ግን በምድረ በዳ ከአራዊት ጋር ሳይጣሉት የበረኃ ማርና አንበጣ እየተመገበ የግመል ጠጉር ለብሶ ያን ዕድሜ በእግዚአብሔር ጥበቃ መገኘት የሚገርምም የሚደንቅም ነው።

ዮሐንስ የተወለደው ለቤተሰቡ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ነበር ስለቤተሰቡ ሁኔታ የሚያውቀው አልነበረም። ከእናቱ ማኅጸን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ የሞላበት ሰው ነበርና ኑሮው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ነበር። ሴቶች ከወለዷቸው ሁሉ ዮሐንስ መጥምቅን የሚበልጠው አልተነሣም ብሎ ጌታችን ተናግሮአል።

ዮሐንስ በኤልያስ መንፈስ የሚሄድ ኤልያስ በአመንዝራይቱ በኤልዛቤል እንደተሳደደ ዮሐንስም በአመንዝራይቱ በሄሮድያዳ ልጅ መከራ ተቀብሏል። ሁለቱም ንጉሥና ንግሥት ገስጸዋል አስተምረዋል።

መጥምቁ ዮሐንስ ሴቶች ከወለዷቸው ሁሉ እሱን የሚበልጥ አልተነሣም። ዮሐንስ ግን እንዲህ አለ "ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ከእኔ በፊት ነበረና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኗል" "እኔ የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ የሚከብር ይህ ነው" "እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል" ሲል ክርስቶስ ከእርሱ እንደሚበልጥ በአጽንዖት ተናገረ። ጌታችንም "በመንግሥተ ሰማያት ግን የሚያንሰው ይበልጠዋል" ብሏል። ቅዱስ ዮሐንስ ስለክርስቶስ ማንነት በግልጥ የተረዳ ስለነበር ጌታችን ሊጠመቅ ሲሄድ እንኳ እኔ ባንተ ልጠመቅ ይገባኛል አንተ ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሏል። መሢሑን ለመቀበል የተዘጋጀ ልብ አልነበራቸውም እንጂ እንደ መንገድ ጠራጊ ሆኖ ስለክርስቶስ እየሰበከ የእግዚአብሔር የማዳን ቀን እንደተገለጠ አስረግጦ አስተምሮአል።

ቅዱስ ዮሐንስ አባቱ ካህን መሆኑ የካህናት ዘር መሆኑን ያስረዳል። እናቱም "ከአሮን ልጆች ነበረች" ስለሚላት በእናቱም በአባቱም የካህናት ዘር ነበር። ድንግል ማርያምም የኤልሣቤጥ ዘመድ ስለሆነች የካህናት ዘር መሆኗን መረዳት ይቻላል። በእርግጥ ለዚህ የተባረከ ታሪክ ያበቃቸው የካህናት ዘር መሆናቸው አይደለም። የካህናት ዘር መሆናቸው ያበረከተው አስተዋጽዖ ፈጽሞ የለም። ዮሐንስ ከሁሉም ነቢያት ለየት ያለ ክብር ያለውና የነቢያት መደምደሚያ የሐዋርያት መጀመሪያ ነው።

እርሱ "ከእሥራኤልም ልጆች ብዙዎችን ወደጌታ ወደአምላካቸው ይመልሳል እርሱም የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዳ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ

ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል" (ሉቃ. 1÷16)። ተብሉ የተነገረለት ታላቅ ነቢይ ነው። ነቢዩ ሚክያስ በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር "እነሆ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደልጆች የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል" (ሚክ. 4÷5) ብሏል። ስለዮሐንስ መናገሩ ነበር ኤልያስና ዮሐንስ የተገዙበት ኃይለ እግዚአብሔር ተመሳሳይ ስለነበር ሚክያስ ኤልያስ እያለ ዮሐንስን ጠርቷል።

የጌታችን ደቀመዛሙርት በደብረ ታቦር ተራራ ብርሃነ መለኮቱን ሲገልጥላቸው በድንጋጤ ፅለተ ምጽአት የደረሰ ስለመሰላቸው "እንግዲህ ጻፎች ኤልያስ አስቀድሞ ሊመጣ ይገባዋል ስለምን ይላሉ?" ብለው ጠይቀው ነበር። ጌታችንም ሲመልስ "ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል ሁሉንም ያቀናል ነገር ግን እላችኋለሁ ኤልያስ ከዚህ በፊት መጣ የወደዱትንም ሁሉ አደረጉበት እንጂ አላወቁትም" አላቸው። "በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ስለመጥምቁ ዮሐንስ እንደነገራቸው አስተዋሉ" ይላል (ማቴ. 17÷10-13)።

•

ዮሐንስ በነበረበት ዘመን ንጉሥ ሄሮድስ በገሊላ ይገዛ ነበር። በዚያን ጊዜም የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ቀምቶ (ሄሮድያዳን) አግብቶ ነበር። ዮሐንስም "ኢይደልወከ ታውስብ ብእሲተ እኁከ ፊልጶስ" የወንድምህን የፊልጶስን ሚስት ታገባ ዘንድ አይገባህም። በማለት ዘለፈው መከረው ገሰጸው በዚህም ሄሮድስና ሄሮድያዳ አዘኑ ተቆጡ የሄሮድስ የልደት በዓል በሆነበት ጊዜ የሄሮድያዳ ልጅ በሄሮድስ ፊት ዘፈነች ንጉሡንም አስደሰተችው እስከመንግሥቱ እኩሌታም ድረስ ሊሰጣት እንድትለምነው ጠየቃት፣ እርሷም ከእናቷ ጋር ተማክራ የዮሐንስን አንገት እንዲሰጣት ጠየቀችው በነገሩ ባይደሰትም

ስለመሐላው ቆርጦ ሰጣት በድኑንም ደቀመዛሙርት ወስደው ቀበሩት (ማቴ. 14+1-12) ።

## በቤተ-ክርስቲያናችን ሰዎች

### ( ስለ ዮሐንስ የተሰጠ የሐሰት ትምህርት )

ወንጌላውያን ስለዮሐንስ ሲጽፉ መንፈስ ቅዱስ የገለጠላቸውንና የሚያውቁትን እውነት ብቻ ጽፈዋል። ስለቅዱሱ ታሪክ ከመንፈስ ቅዱስ ተሰውሮ የቀረብን ነገር ናሮ ለእኛ የተገለጠልን ነገር የለም። በመሆኑም ስለዮሐንስ ከዚህ በላይ የምንለው አይኖረንም ቤተ-ክርስቲያን ግን "የሄሮዳያዳ ልጅ የዮሐንስን አንገት በወጭት ይዛ ስትሄድ ክንፍ አውጥቶ ፊቷን በክንፉ ጸፍቷት በረረ እየዞረም 15 ዓመት አስተማረ" ብለዋል።

አንድም ይሉና "ወስዳ ለእናቷ ሰጠቻት እናቷም ንጉሥና ንግሥት ትዘልፍ የነበረች አንደበት እያለች ትሰፋ ነበር ቢሉ በመርፌ ትፈትል ነበረ ቢሉ በወስፌ ዓይኑን ስትወጋው በክንፉ ፊቷን ጸፍቷት ወጥቶ 15 ዓመት አስተማረ" ብለዋል። ሐሰት ነው ብንልም ለእግዚአብሔር ምን ይሰነዋል እንባላለን። ለእግዚአብሔር ምን ይሰነዋል በሚለው ፊሊጣችን ባንዋሽ በጉ ነበር። እውነቱን ብቻ እየመሠከርን ብናገለግል ለበረከት ይሆንልናል።

## ስግደት ለመላእክት

### ሐመር 5ኛ ዓመት ቁጥር 1

በማኅበረ ቅዱሳን ሥር በየሁለት ወሩ የሚታተመው ሐመር መጽሔት ስግደት ለመላእክት በሚለው ርእስ ሥር በገጽ 12 ላይ የሚከተለውን አስፍሮአል። "ለእግዚአብሔር በመንፈስ የአምልኮ ስግደት

እንደምንሰግድ ሁሉ እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ሁሉ አብረው ለሚገኙት ቅዱሳን መላእክትም የአጋ ስግደት በእምነት ማቅረብ ይገባል እነርሱም እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ሁሉ አሉና" ብሏል። መጽሔቱ ባሰፈረው ምንባብ ውስጥ ሁለት ዓበይት ክህደቶችን እንመለከታለን። እነርሱም

1ኛ እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ሁሉ መላእክትም እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የመገኘት ችሎታ እንዳላቸው አድርጉ ማቅረቡ ነው። መቼም ቢሆን እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው እርሱ ባለቤቱ ቅሉ "እንመሳሰል ዘንድ ከማን ጋር ታስተያዩኛላችሁ?" ብሏል (ኢሳ. 46፥5)። እግዚአብሔርን የሚመስል እርሱንም የሚገዳደር እንደእርሱም የሆነ ከቶ አልነበረም፣ አይኖርምም። አምልኮ፣ ስግደት፣ ዝማሬ፣ ምሥጋና ሁሉ የእርሱ የብቻው ነው። ከእርሱ በስተቀር ያልተፈጠረ አንድም ነገር የለም። ሁሉም የእጁቹ ሥራዎች ናቸው። መላእክት የእርሱ ፍጥረቶችና ለምሥጋና ለተልዕኮ የተመደቡ የልዑል ባሪያዎች ናቸው። እርሱ ወደ ወደደው ለምህረትም ለመዓትም ይልካቸዋል። በአንዳችም ነገር ከትዕዛዙ ዝንፍ አይሉም መዝሙረኛው ዳዊት "ቃሉን የምትፈጽሙ ብርቱዎችና ኃያላን የቃሉንም ድምጽ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ እግዚአብሔርን ባርኩ" ብሏል (መዝ. 102*20)።

የመላእክት ጌታ የሆነው እግዚአብሔር ክብርንና ውዳሴን ከመላእክት እየተቀበለ በሁሉ ቦታ ከሰማያትም በላይ ባለ ሰማይ ከምድርም በታች ባለው ሁሉ ሳይታጣ ምሉዕ በኩለሄ ሆኖ የሚኖር ነው፣ እግዚአብሔር ረቂቅ መንፈስ በመሆኑና ሁሉንም መሆንና ማድረግ የሚችል እግዚአብሔር ስለሆነ የትም ይገኛል። በቦታ አይታጣም፣ ለፍጥረቱ ሁሉ በእያንዳንዱ ፊት የመገኘት ብቃትና ሥልጣን አለው። መላእክት ረቂቃን መናፍስት በቦታ የተወሰኑ ነገር ግን ፈጣኖችና ፈጥኖ ደራሾች ናቸው። መላእክት እንደ እግዚአብሔር

በሁሉ ቦታ የመገኘት ችሎታ የላቸውም። ቅዱስ ገብርኤል "እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ" አለ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ማለቱ የእግዚአብሔር ፊት በሁሉ ቦታ እንደሆነ ሁሉ እኔም በሁሉ ቦታ እገኛለሁ የሌለሁበት ቦታ የለም ማለቱ ነው ብለን ከተረጐምነው እጅግ ወደ ጥልቅ ክህደት እንገባለን።

የመላእክት ፊታቸው ወደ አንድ ገጽ የዞረ ነው እግዚአብሔር ደግሞ ፊቱ በሁሉ ቦታ ነው። እንግዲያው የእግዚአብሔር ፊቱ በቦታ ሁሉ ከሆነ ፍጥረት ሁሉ በፊቱ ነው ማለት ነው። ይህም መላእክትን ሁሉ ያካተተ ነው። የቅዳሴ መጽሐፍም "ኩሉ ስጡህ በቅድሜሁ" ማለትም በእርሱ ፊት ሁሉ የተገለጠና የተራቆተ ነው ማለት ነው። ስለዚህም ሁላችን እንደ ገብርኤል እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው እገሌ ነኝ የማለት ድፍረት አለን። ምክንያቱም በእያንዳንዳችን ፊት እግዚአብሔር አለና። በመሆኑም መላእክትን በእግዚአብሔር ፊት እንዲገኙ ያደረጋቸው የእግዚአብሔር ፊት በሁሉ ቦታ መገኘት እንጂ የመላእክት ምሉዕ በኩለሄነት አይደለም። መላእክት እንደፈጣሪ በሁሉ ቦታ የሚገኙ ከሆነ እግዚአብሔር ለእነሱ የሚሰጠው ደረጃ በጣም ዝቅተኛ ነው። [illegible] የተሻለ እግዚአብሔር የለንም። ፍጥረት የሚተካከለው እግዚአብሔር ከሆነ ኃይሉም ጥበቡም ውሱን ነው። እግዚአብሔር ግን እንደዚህ አይደለም።

2ኛ ደግሞ ለእግዚአብሔር በመንፈስ እንደምንሰግድ ለመላእክትም እንሰግዳለን የሚል ነው። በየትኛውም ሥፍራ ሆነን ወደ ማንኛውም አቅጣጫ ለእግዚአብሔር ስንሰግድ በሁሉም ቦታ የሚገኘው አምላካችን ስግደታችንን ስለሚቀበል ነው። እግዚአብሔር እስኪገለጥ

ድረስ እንጠብቅም እርሱ የሌለበት ቦታ ስለሌለ በመንፈስ ያለውን እርሱን በስግደት እናከብራለን። ተገለጠም አልተገለጠም በዚህ ወይም በዚያ ከዚህ ወይም ከዚያ ስለማይባል እርሱን በሰገድንበት ቦታ ሁሉ እናገኘዋለንና በፊታችን ለማይታጣው እንግዚአብሔር እንሰግዳለን።

መላእክት ግን እንደዚህ አይደሉም። ከዚህ ወይም ከዚያ ናቸው እንጂ እንደ አምላካቸው በሁሉ ቦታ ስለማይገኙ በዘፈቀደ እንሰግድም። ለእነርሱ ለመስገድ ካስፈለገ የግድ እንደ ወንጌላዊ ዮሐንስና ሌሎችም ቅዱሳን መገለጣቸውን መጠበቅ አለብን። ላልተገለጠልን መልአክ በድፍረት ብንሰግድ አምልኮ ባዕድን እየተለማመድን እንደሆነ መገንዘቡ ጤናማ አመለካከት ነው። በቅዱስ መጽሐፍ የተጠቀሱት ሁሉ ለመላእክት የሰገዱት በተገለጡላቸው ጊዜ ብቻ መሆኑ ለዛሬው ስግደታችን ጥንቃቄ እንድናደርግ በእጅጉ ያግዘናል። ደግሞም ቅዱስ መጽሐፍ ስለስግደት የአምልኮ የጸጋ፣ የአክብሮት በማለት እንዳልደለደለ እየታወቀ ዛሬ ማለዳ በተፈጠረ የስግደት ዓይነት ሕዝባችንን ጠፍረን አሥረን ወደሞት መጉተታችንን በብዙ ነፍሳት ተጠያቂዎች ያደርገናል።

ዮሐንስ የሰገደው ስግደት ምን አይነት ስግደት እንደሆነ ያልታወቀውን እንዲህና እንዲያ ብለን ማብራሪያ ከመስጠት ብንቆጠብ መልካም ነው። ምንም አይነት ስግደት ይሁን ዮሐንስ ለተገለጠለት መልአክ ተደፍቶ ሰግዷል። መልአኩም ቢሆን ስግደቱን ያልተቀበለው ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባው ስግደት ለእርሱም ስለቀረበለት ነው ለእግዚአብሔር ስገድ እኔ እንደ አንተ ባሪያ ነኝ ማለቱ ዮሐንስም ሆነ መልአኩ ለእግዚአብሔር እኩል ባሪያዎች መሆናቸውን ያስረዳል እንጂ የትሕትና ጉዳይ ፈጽሞ የለበትም።

እንግዲህ ስግደቱን በይገባቸዋል ብንቀበለው እንኳ እንደተጻፈው በተገለጡበት ሰዓት ቢሆን ይመረጣል። ፈቃዳቸው ከሆነም ይቀበሉታል፣ ካልሆነም እንዳታደርገው ተጠንቀቅ እንባላለን። ከዚህ አልፈን ባለሙያ በተጠበበበትና ሰባቱ ቀለማት ባስዋቡት የጨርቅና የወረቀት ሥዕል ፊት በመቆም ለሌለ መልአክ ብንሰግድ ከንቱና አጋንንታዊ ልምምድ ይሆንብናል። ከሥዕል አፍ ቃል ወጣ ድምጽ ተሰማ የሚሉት ማደናገሪያዎች ማንበብና መጻፍ ለማይችለው ሕዝባችን የሞት መንገድ በመሆናቸው ከእንግዲህ እርም ብለን ብናቆምና ስብከታችንን ብናስተካክል መልካም ነው። ትናንት ያበላሸነውን ዛሬ ለማስተካከል ቢያስቸግረንም የገደልነውን ሕዝብ እኛው ማዳን አለብን ሞትም ሕይወትም በእጃችን አለና።

እንግዲህ አባቶቻችን ባቆዩን ትምህርት ጸንተን ለእግዚአብሔር የሚገባውን ለእግዚአብሔር ለመላእክትም የሚገባውን ለመላእክት በመስጠት ለይተን ልናመልክና ልንሰግድ ይገባናል። ለመላእክትም ፈርተንና ደንግጠንም ቢሆን ወይም ይገባቸዋል ብለን መስገድ ያለብን እንደ አባቶቻችን እንጂ በእንግዳ ትምህርትና በባዕድ አምልኮ ተወስደን አይደለም። ደግሞም በታላት ላይ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል። ዮሐንስ ለመልአኩ የሰገደው በምዕራፍ 22÷8 ላይ ብቻ እንጂ በሌላ ቦታ አልሰገደም ቃሉ "ይህንም ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ በሰማሁትና ባየሁትም ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልአኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ" ሲል ለመልአኩ እየሰገደ መሆኑን ገልጧል።

በራእይ 19÷9-10 ያለው ክፍል ደግሞ "እርሱም ወደ በጉ ሠርግ እራት የተጠሩ ብጹዓን ናቸው ብለህ ጻፍ አለኝ ደግሞም ይህ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ነው አለኝ። ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋሁ እርሱም እንዳታደርገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር የኢየሱስም ምሥክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ለእግዚአብሔር ስገድ የኢየሱስ ምሥክር የትንቢት መንፈስ ነውና አለኝ" ይላል። ይህ

ደግሞ ዮሐንስ ለመልእክቱ ሳይሆን ለሌላ ለትንቢት መንፈስ የሰገደ እንደሆነ ይገልጣል። ቢሆንም ስግደቱ ግን በሁለቱም ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም። እኛም ተቀባይነት የሌለውን ስግደት ከመስገድና ከማሰገድ ብንቆጠብ እጅግ ብልህነት ነው።

በአንጻሩም ደግሞ ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልእክ መስሎ እየተገለጠ እንድንሰግድለት የይገባኛል ጥያቄ በማቅረቡ ሳንለየውና ሳንረዳው በመስገዳችን የባሰ ጉዳት ስለምናመጣ ለሕይወታችን ራሳችን ብንጠነቀቅ መልካም ነው።

በተረፈ ግን መላእክት እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ይገኛሉ ምሉዕ በኩለሄ ናቸው፣ ስግደትም እንዲሁ ይገባቸዋል የሚለው የኑፋቄ ትምህርት ከቀደምት አበው ሐዋርያት ያልተገኘ የክህደትና የርኩሰት ትምህርት በመሆኑ ልንርቀውና ልንሸሸው ይገባል። የዚህ የሐሰር መጽሔት አዘጋጅም ቢሆን የራሱን እንግዳ ትምህርት ከመልፈፍ ይልቅ ምሥጢር አደላድሎ ጉባኤ ውሎ ፍጡርና ፈጣሪን ለይቶ ነው እንጂ እንዲሁ ኢአርቶዶክሳዊ ትምህርት ማቅረብ የለበትም።

አሁን አሁን 12ኛ ክፍል መጨረስና ከዮኒቨርስቲ መመረቅ እንደመመዘኛ እየተቆጠረ ይመስላል በዚህ ማኅበር ውስጥ የታቀፉ ሠራተኞች ምንም ያሬዳዊ ትምህርት ሳይኖራቸው ዲቁና የተቀበሉ ብዙዎች ናቸው። ዲቁና ብቻውን ዕውቀት አይሆንምና ወደ ሊቃውንቱ ጉራ ብሎ ምሥጢር መስማቱ ደግሞ የተሻለና አማራጭ የማይገኝለት ነገር ነው። ከዚህ አልፎ ደግሞ እገሌ መናፍቅ እገሌ ተሐድሶ በማለት ስም ማጥፋቱ እኛ ልንጮኽው ሆኖ ሳለ ጩኸቱን ቀመኝ አይነት ሆኖብን ዝም ብለናል።

"ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ" (ማቴ. 4÷10)